



# በአርብቶ አደር አካባቢዎች የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አተገባበር መመሪያ



**ትምህርት ሚኒስቴር**
**ሚያዝያ 2002 ዓ.ም**

## ማ ው ጫ


| | ር ዕ ስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 1 | **መግቢያ**................................................ | 1 |
| 2 | የአርብቶ አደር አካባቢዎች ሁኔታ ትንታኔ.................. | 3 |
| | 2.1. የአጠቃላይ ሁኔታ ትንታኔ..................... | 3 |
| | 2.2. የትምህርት ሁኔታ ትንታኔ.............. | 6 |
| 3 | የቁልፍ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦች ትርጉምና ማብራሪያ..................... | 12 |
| 4. | የተንቀሳቃስ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ባሕሪያትና የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች............... | 15 |
| 5 | የመመሪያው ዓላማዎች.............................. | 21 |
| **6** | **የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት** | 22 |
| | 6.1. መርሀ ትምህርት፣ የትምህርት ደረጃና የትምህርት ዓይነቶች... | 22 |
| | 6.1.1 መርሀ ምህርት........................ | 22 |
| | 6.1.2 የትምህርት ደረጃና ትምህርት የማጠናቀቂያ ጊዜ... | 22 |
| | 6.1.3 የትምህርት ዓይነት | 25 |
| | 6.2. የመማሪያ- ማስተማሪያ መጻሕፍት......... | 25 |
| | 6.3 የትምህርት መስጫ ቦታና ጊዜ.............................. | 27 |
| | 6.3.1 የትምህርት መስጫ ቦታ............ | 27 |
| | 6.3.2 የትምህርት መስጫ ጊዜ........................... | 28 |
| | 6.4 የትምህርቱ አቀራረብ............ | 32 |
| | 6.5 ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ያጠናቀቁ ተማሪዎች የሚኖራቸው የባሕሪይ ገጽታዎች (Profile) ............................. | 34 |
| | 6.6 የተማሪዎች ምዘናና ሽግግር............... | 36 |
| | 6.6.1 የተማሪዎች ምዘና.................. | 36 |
| | 6.6.2 የተማሪዎች ሽግግር............... | 38 |







| | ር ዕ ስ | ገጽ |
|---|---|---|
| 7. | **የአመቻቾች ምልመላ፣ ሥልጠናና የሥራ ድርሻ...................** | 41 |
| | 7.1 የአመቻቾች መመልመያ መስፈርቶችና የምልመላ አፈፃፀም...... | 41 |
| | 7.2 የአመቻቾች የቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ስልጠናዎች... | 42 |
| | 7.2.1 የቅድመ -ሥራ ስልጠና....................... | 43 |
| | 7.2.2 የሥራ ላይ ስልጠና................................... | 44 |
| | 7.2.3 የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ስልጠና............................. | 46 |
| | 7.3. የአመቻቾች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት.......................... | 46 |
| 8. | **የአመቻቾች ደመወዝና ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች.......................** | 50 |
| 9. | **የትምህርት ድጋፍና ክትትል.....................................** | 51 |
| | 9.1 በክልል ትምህርት ቢሮ ደረጃ.................................. | 51 |
| | 9.2 በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ............................... | 52 |
| 10 | **የባለድርሻዎች ትስስርና አጋርነት...............................** | 55 |
| 11 | **የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አመራር፣ አደረጃጀትና የሕብረተሰብ ተሳትፎ.** | 57 |
| | 11.1 በየደረጃው ያሉ የትምህርት መዋቅር አካላት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት... | 57 |
| | 11.1.1 የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር.................. | 57 |
| | 11.1.2. የክልል ትምህርት ቢሮ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት.............. | 58 |
| | 11.1.3 የዞን ትምህርት መምሪያ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት......... | 60 |
| | 11.1.4 የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት...... | 61 |
| | 11.1.5 የጣቢያ ትምህርትና ሥልጠና አመራር ኮሚቴ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት... | 63 |
| | 11.2. የሕብረተሰብ ተሳትፎ...................... | 65 |

## 1.መግቢያ

ትምህርት ለአንድ ሀገር ሁለንተናዊ ልማት የሚበጁ ዜጐችን ለማፍራት የሚያስችል፣ በህብረተሰቡ ዘንድ የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት የሚረዳ፣ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ ውጤቶችና ሳይንሳዊ ግኝቶች ጋር በማስተዋወቅ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ እድገቶችን የሚያፋጥን መሣሪያ ነው። በሀገራችንም ትምህርትን የልማትና የእድገት መሣሪያ ለማድረግ በ1986 የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ ተቀርፆ ሥራ ላይ ከዋለ ወዲህ የሀገራችን የትምህርት ተሳትፎና ፍትሐዊነት ከፍተኛ እድገት ማሳየቱ የሚታወቅ ነው። ሆኖም ግን ይህ እድገት በሁሉም ክልሎች በተመሳሳይ መልኩ የታየ እንዳልሆነ የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ። በተለይ በአርብቶ አደር አካባቢዎች በየደረጃው የሚታየው የትምህርት ተሳትፎ ከሌሎች ክልሎች ጋር ሲነፃፀር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል።

በዚህም መሠረት የኢፊዲሪ መንግስት በልማት ኋላቀር የሆኑትን የአርብቶ አደሩንና ከፊል አርሶ አደር ክልሎች በልማት ለማገዝ የተለያዩ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ለተግባራዊነቱ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል። ትምህርት ሚኒስቴርም በነዚህ ክልሎች ያለውን ዝቅተኛ የትምህርት ተሳትፎ ለማጐልበት የአርብቶ አደር አካባቢዎች የ1ኛ እና 2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጎልበቻ እስትራቴጂ በመንደፍ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ይገኛል። በስትራቴጂው ውስጥ ከተጠቀሱት የትምህርት ማስፋፊያ ስልቶች ውስጥ አንዱ ተንቀሳቃሽ ትምህርት ሲሆን ታዳሚዎቹም በመደበኛውም ሆነ በቋሚ የትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በሚሰጠው አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ሊስተናገዱ የማይችሉ የአርብቶ አደሩ ሕፃናት ናቸው፤





ምንም እንኳን ተንቀሳቃሽ ትምህርትን በተመለከተ በአገራችን ውስጥ ከቁጥር የሚገባ ተሞክሮ ባይኖርም የሌሎች አገሮችን ተሞክሮ ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አገናዝቦ ተግባራዊ ማድረግ ወቅታዊ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ ት/ ሚኒስቴር ከዩኒሴፍ ባገኘው የፋይናንስ ድጋፍ የተንቀሳቃሽ ትምህርት ፕሮገራምን ለመጀመር የሚያስችል ጥናት በ2001 ዓ.ም በጅጅጋ ዩኒቨርስቲ አስጠንቷል። ጥናቱ ከአፋርና ሶማሌ ክልሎች በቀረበ ጥያቄ መሠረት የተካሄደ ሲሆን ክልሎቹ ወደ ፕሮግራም ትግበራ እየገቡ ነው።

በአሁኑ ጊዜ የአፋር ክልል ት/ቢሮና አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተወሰኑ አካባቢዎች ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም በማካሄድ ላይ ቢገኙም ፕሮግራሙ ለአገራችን አዲስ በመሆኑና የአተገባበር መመሪያ ባለመኖሩ አፈፃፀሙ የተዘበራረቀ ሆኖ ይታያል። ስለሆነም በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውሱን በሆነ ደረጃ በመካሄድ ላይ ያለውንና ወደፊትም በስፋት የሚካሄደውን ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም አፈፃፀም ወጥነት ያለው፣የተቀናጀና ውጤታማ ለማድረግ ይህን መመሪያ ማዘጋጀት አስፈልጓል። መመሪያው የአርብቶ አደር አካባቢዎችን አጠቃላይ ነባራዊ ሁኔታ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀ በመሆኑ ጉዳዩ የሚመለከታቸው የክልል ትምህርት ቢሮዎች ከክልላቸው አርብቶ አደር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥመው ሥራ ላይ ማዋል ይጠበቅባቸዋል።

## 2. የአርብቶ አደር አካባቢዎች ሁኔታ ትንታኔ

### 2.1. የአጠቃላይ ሁኔታ ትንታኔ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በአርብቶ አደርነት ተለይተው የሚታወቁ አካባቢዎች የአፋር ክልል፣ የሶማሌ ክልል፣በኦሮሚያ

ክልል የሚገኙ 33 ወረዳዎችና በደ/ብ/ብ/ሕዝቦች ክልል የሚገኙ 7 ወረዳዎች ናቸው። እነዚህ አካባቢዎች ከባሕር ወለል 1500 ሜትር በታች ከፍታ የሚገኙ ደረቅና ከፊል ደረቅ የአየር ንብረት ያላቸውን ረባዳ ቦታዎች የሚያካትቱ ሲሆን ከአገሪቱ ጠቅላላ ቆዳ ስፋት 61% የሚሆነውን ይሸፍናሉ ተብሎ ይገመታል።

እንደ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን የ2000 ዓ.ም የሕዝብና ቤቶት ቆጠራ መረጃ የኢትዮጵያ አርብቶ አደር ሕዝብ ብዛት 10 ሚሊዬን ይደርሳል። ይህም ከአገሪቱ ጠቅላላ ሕዝብ ብዛት የ12.5% ያህል ድርሻ አለው። ከጠቅላላው የኢትዮጵያ አርብቶ አደር ህዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆነው በአፋርና በሶማሌ ክልሎች ውስጥ ይኖራል።

በሌላ በኩል አርብቶ አደሩ በተንቀሳቃሽ፣ በከፊል ተንቀሳቃሽና በቋሚ አስፋፈር ኑሮውን ይመራል። አሰፋፈሩ በጣም የተበታተነ ሲሆን በአንድ ካሬ ኪሎሜትር ውስጥ የሚኖረው ሕዝብ ብዛት በአገሪቱ ውስጥ የመጨረሻው ዝቅተኛ ከሚባሉት የሚመደብ ነው። ለምሳሌ ያህል በአገር አቀፍ ደረጃ በአንድ ካሬ ኪሎሜትር ይኖራል ተብሎ የሚገመተው አማካይ የሕዝብ ብዛት 60 ሲሆን በአፋርና በሶማሌ ክልሎች ግን በቅደም ተከተል 12.2 እና 11 ብቻ ነው።

የአርብቶ አደሩ ሕዝብ ኑሮ ኋላቀር በሆነ የእንስሳት እርባታ ላይ የተመሠረተ ሲሆን የእንስሳት ሀብቱም የቀንድ ከብትን፣ ግመልን፣ በግን፣ ፍየልንና የጋማ ከብትን በአበይትነት ያካትታል።

የአርብቶ አደር አካባቢዎች ዓመታዊ የሙቀት መጠን ባመዛኙ ከፍተኛ፣





የሚያገኙት ዓመታዊ የዝናብ መጠን አነስተኛና የማያስተማምን በመሆኑ አካባቢዎቹ ለተደጋጋሚ ድርቅ ብሎም ለውሀና ግጦሽ እጥረት የተጋለጡ ናቸው ። ስለሆነም አርብቶ አደሩ የሕልውናው መሠረት ለሆኑት እንስሳት ውሀና ግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ቦታ የሚያደርገው እንቅስቃሴ የአኗኗሩ አይነተኛ መገለጫ ሆኖ ቆይቷል። አርብቶ አደሩ ከቦታ ቦታ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ድግግሞሽና የጊዜ እርዝማኔ እንደ አየር ንብረቱ ይለዋወጣል። በመደበኛው የአየር ንብረት ሁኔታ በበጋና በክረምት ወቅቶች የሚደረገው እንቅስቃሴ በውል ወደሚታወቁ ቦታዎች ሲሆን የሚንቀሳቀሱትም በአብዛኛው ወንድ ወጣቶችና ጎልማሶች ብቻ ናቸው። በድርቅ ወቅት ግን ሁሉም የቤተሰብ አባላት ከ100 ኪሎ ሜትር ያላነሰ ተጉዘው የድርቁን አደጋ ያሳልፋሉ። ድርቁ የከፋ ከሆነም ወደ አጎራባች ሀገሮች ገብተው የተወሰነ ቆይታ ያደርጋሉ።

የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች ከአገሪቱ ጠቅላላ የከብት ሀብት 24 በመቶ ያህል ድርሻ እንዳላቸው ቢገመትም ከጥራት ይልቅ በብዛት /ቁጥር/ ላይ በሚያተኩረው ኋላቀር የእንስሳት እርባታ ዘዴ ምክንያት አርብቶ አደሩም ሆነ አገሪቱ የሚፈለገውን ያህል ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቆይተዋል። የእንስሳት እርባታ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ዋነኛ መተዳደሪያና የኢኮኖሚ መሠረት ቢሆንም እንደ አዋሽ፣ ዋቢሸበሌ፣ ገናሌ፣ ዳዋና ኦሞ ወንዞች ዳርቻና የተሻለ ዓመታዊ የዝናብ መጠን በሚያገኙ አንዳንድ ቦታዎች የሚኖሩ ከፊል አርብቶ አደሮች በአነስተኛ ማሳና ኋላቀር በሆነ የአስተራረስ ዘዴ በቆሎ፣ ማሽላ፣አትክልትና ፍራፍሬ ያመርታሉ። ባሕላዊ በሆነ መንገድ እንደ እጣንና ሙጫ ያሉ የደን ውጤቶች ማምረት፣ ባሕላዊ የንብ እርባታና አሳ ማስገር በሶማሌ ክልል፣ በኦሮሚያና በደ/ብ/ብ/ህዝቦች ክልል አንዳንድ የአርብቶ አደር አካባቢዎች

የሚታዩ አነስተኛ ኢኮኖሚያዊ ክንውኖች ናቸው። ከዚህም በተጨማሪ የአርብቶ አደር አካባቢዎች በጥናት የተረጋገጡና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ እንደ ወርቅ፣ ፕላቲኒየም፣ታንታሊየም፣ እብነበረድ፣ የተፈጥሮ ጋዝ፣ ፔትሮሊየም፣ ብረትና ፖታሺየም ያሉ ውድ ማእድናት ክምችት አላቸው። ባለፉት ጨቋኝ መንግሥታት የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች ከሌሎች የአገራችን ክፍሎች በባሰ መልኩ ከማንኛውም የልማት እንቅስቃሴዎች ተገልለውና ተዘንግተው የመኖራቸውን ያህል አንፃራዊ በሆነ ዝቅተኛ የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። በአሁኑ ጊዜ እነዚህ አካባቢዎች መንግሥት የተመጣጠነ ልማትን በመላ ሀገሪቱ እውን ለማድረግ የዘረጋው የልዩ ድጋፍ ሥርዓት ግንባር ቀደም ተጠቃሚዎች ሲሆኑ በሁሉም የልማት ዘርፎች ከምንጊዜውም በተሻለ የእድገት እርምጃ ላይ ናቸው።

በሌላ በኩል የአርብቶ አደር አካባቢዎች ለከፋ የብሄረሰብ ጭቆና ተዳርገውና ከማንኛውም የፖለቲካ ተሳትፎ ተገልለው ለረዥም ዓመታት ኖረዋል። ነገር ግን በአገራችን ዴሞክራሲያዊና ፌዴራላዊ የፖለቲካ ሥርዓት ከሰፈነ ወዲህ አርብቶ አደሩ ሕዝብ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበት፣ በቋንቋው የሚማርበትና የሚዳኝበት፣ በማንነቱና በባሕሉ የሚኮራበትና በአካባቢው የልማት እንቅስቃሴ በንቃት የሚሳተፍበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል።

## 2.2. የትምህርት ሁኔታ ትንታኔ

የአገራችን የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ በ1986 ዓ.ም ተቀርፆ ተግባራዊ ከሆነ ወዲህ በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች በተለይም በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት





አመርቂ ውጤቶች መመዝገባቸው እሙን ነው። ይሁንና የአርብቶ አደር አካባቢዎች የትምህርት ዘርፍ ልማት ከሌሎች የአገራችን ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር ገና በአነስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል። ለአብነት ያህል በ2000 ዓ.ም በአገር አቀፍ ደረጃ የተመዘገቡትን የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ምጣኔዎች በዚያው ዓመት በአፋርና በሶማሌ ክልሎች ከተመዘገቡት ጋር ሲነፃፀሩ ምን ያህል ሰፊ ልዩነት እንደነበራቸው ከሚከተለው ስታቲስቲካዊ መረጃ መረዳት ይቻላል።

| | **የመጀመሪያ ደረጃ ጥቅል ተሳትፎ** | | | **የሁለተኛ ደረጃ ጥቅል ተሳትፎ (በ%)** | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **ጥቅል ተሳትፎ** | **ወንድ** | **ሴት** | **ጥቅል ተሳትፎ** | **ወንድ** | **ሴት** |
| አገር አቀፍ | 95.6 | 100.5 | 90.5 | 37.1 | 44.4 | 29.6 |
| ሶማሌ ክልል | 32.7 | 34.9 | 29.6 | 4.1 | 5.3 | 2.3 |
| አፋር ክልል | 26.2 | 29.0 | 22.2 | 7.8 | 8.1 | 7.3 |

ከፍ ብሎ ከተመለከተው ከፍተኛ የትምህርት ተደራሽነት ችግር ባሻገር በአርብቶ አደር አካባቢዎች የሚሰጠው ትምህርት ጥራት፣ ተገቢነትና ብቃት ከሌሎች የአገራችን ክፍሎች ጋር ሲነፃፀር በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ መሆናቸውን የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ዝቅተኛ የትምህርት ልማት ደረጃ መንስኤ የሆኑ ምክንያቶች በርካታ ናቸው። የመጀመሪያው መሠረታዊ ምክንያት እነዚህ አካባቢዎች ከሌሎቹ የአገራችን

ክፍሎች በከፋ መልኩ የትምህርት አገልግሎት ተነፍገው ለዘመናት መኖራቸው ነው። ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከአርብቶ አደሩ ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ ጋር የሚጣጣሙ የትምህርት አቅርቦት መንገዶችን ነድፎ ሥራ ላይ ለማዋል ጥረት ሳይደረግ መቆየቱ ነው።

በእርግጥ በአገራችን ውስጥ ዴሞክራሲያዊና ፌዴራላዊ የሆነ የመንግሥት ሥርዓት እውን መሆን በፈጠረው ምቹ ሁኔታ በርካታ መደበኛ ት/ቤቶችን በአርብቶ አደር አካባቢዎች በመገንባትና መሠረታቸው ከደጋው የአገሪቱ ክፍሎች የሆኑ መደበኛ መምህራንን በመመደብ ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል። ነገር ግን በአንድ በኩል የተገነቡት ት/ቤቶች ቁጥር የትምህርት እድል ካላገኙት እጅግ በርካታ ሕፃናት አንፃር ሲታይ በጣም አነስተኛ በመሆኑ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በቋሚ አሰፋፈር ለሚኖረው ደገኛው የሕብረተሰብ ክፍል ይበልጥ ተስማሚ የሆነው መደበኛ የትምህርት አቅርቦት ሥርዓት አርብቶ አደሩ ከሚገኝበት ተፈጥሯዊ አካባቢ፣ ካለው ባሕልና ተንቀሳቃሽ የኑሮ ሁኔታ ጋር ባለመጣጣሙ የተገነቡት ት/ቤቶችም ቢሆኑ በአብዛኛው በተማሪ እጦት ምክንያት የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘት አልቻሉም። ለምሳሌ ያህል በመጀመሪያው አምስት ዓመት የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም /በ1989 ዓ.ም በቅደም ተከተል 11.6% እና 8.4% የነበረውን የሶማሌ ክልልና የአፋር ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ጥቅል ተሳትፎ ምጣኔ በእቅድ ዘመኑ መጨረሻ (1994 ዓ.ም) ወደ 25% ለማሳደግ ግብ ተጥሎ የተገኘው ውጤት ግን በሶማሌ ክልል 13.1%፣ በአፋር ክልል 12.6%፣ የሴቶች ትምህርት ተሳትፎ ደግሞ በቅደም ተከተል 9.5% እና10.8% ብቻ ነበር። የሁለቱን ክለሎች አማካይ አሀዞች በዚያው ዓመት በአገር አቀፍ ደረጃ በሁለቱም ፆታዎች ከተመዘገበው የ61.6% አማካይ ተሳትፎና 51.2% የሴቶች





ትምህርት ተሳትፎ ጋር ሲነፃፀሩ በ5 እጅ ያህል እንደሚያንሱ መገንዘብ ይቻላል።

ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ዝቅተኛ የትምህርት ዘርፍ ልማት በመንስኤነት ከሚጠቀሱት ሌሎች ምክንያቶች መካከል ተደጋጋሚ ድርቅ፣ ድህነት፣ በቤተሰብ ዘንድ የሕፃናትን ጉልበት በመፈለግ ት/ቤት አለመላክ፣ የት/ቤት ርቀት፣ የመሠረተ ልማት አለመስፋፋት፣ ሥር ሰደው የኖሩ ኋላቀርና ጎጂ አመለካከቶችና ድርጊቶች በዓበይትነት የሚጠቀሱ መሆናቸውን ትምህርት ሚኒስቴር፣ ዩኔስኮና ዩኒሴፍ በጋራ ያካሄዱት የኢትዮጵያ አርብቶ አደር ትምህርት ጥናት ያመለክታል።

በአገራችን ለአርብቶ አደር አካባቢዎች ትምህርት ልማት አዲስ ምዕራፍ የተከፈተው በመጀመሪያ አምስት ዓመት የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም መጨረሻ ነበር ማለት ይቻላል። ቀደም ሲል ለማሳየት እንደተሞከረው በፕሮግራሙ የዕቅድ ዘመን ፍፃሜ በአፋርና በሶማሌ ክልሎች የተገኘው አነስተኛ የትምህርት ተሳትፎ ውጤት በመደበኛው የትምህርት አቅርቦት መንገድ ብቻ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን ህፃናት መሠረታዊ የትምህርት ፍላጐት ማሟላት እንደማይቻል መንግሥትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በውል እንዲገነዘቡ ያደረገ እውነታ ነበር። ስለሆነም በፕሮግራሙ የማጠቃለያ ግምገማ ሪፖርት ለአርብቶ አደሩና ትምህርት ላልተዳረሰባቸው ሌሎች ሩቅ የገጠር አካባቢዎች አማራጭ የትምህርት አቅርቦት ስልቶች ተጠንተው ሥራ ላይ እንዲውሉ በቀረበው የመፍትሄ ሀሳብ መሠረት የተለያዩ የፖሊሲ ጥናቶች በትምህርት ሚኒስቴርና **USAID /BESO Project** ተካሄደ። ከእነዚህ

ጥናቶች ግንባር ቀደሙ "Alternative Routes to Basic Primary Education" በሚል ርዕስ የተካሄደው ሲሆን የጥናቱ ግኝቶች አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአገራችን ትምህርት ሥርዓት አካልና የመንግሥት ፕሮግራም ሆኖ ሥራ ላይ እንዲውል መሠረት ጥለዋል።

በዚህም መሠረት የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴርና ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክልል ትምህርት ቢሮዎች ከአርብቶ አደሩ ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም በጋራ ነድፈው በአርብቶ አደር አካባቢዎች ተግባራዊ በማድረግ በአጭር ጊዜ ውስጥ አበረታች ውጤት ማስገኘት ችለዋል። በተለይም መንግሥት የ4ቱን ታዳጊ ክልሎች ሁለገብ ልማት የማፋጠንና ከሌሎች ክልሎች የልማት ደረጃ ጋር የማመጣጠን ራዕዩን በተግባር ለመተርጎም በፌደራል ደረጃ የልዩ ድጋፍ ቦርድ ካቋቋመ ወዲህ ትምህርት ሚኒስቴር በቦርድ አባልነቱ የእነዚህን ክልሎች የትምህርት ዘርፍ ልማት በሁሉም የትምህርት ደረጃዎች ለማፋጠን የሚያስችል የልዩ ድጋፍ መርሀግብር ዘርግቶ በመተግበር ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት ሚኒሰቴር መ/ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ክልሎችና ሌሎች ባለድርሻዎች በማሳተፍ የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የትምህርት ችግሮች በተጨባጭ ሊያቃልል የሚችል የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ለመጀመሪያ ጊዜ አዘጋጅቶ ሥራ ላይ እንዲውል ከማድረጉም በላይ በራሱ ባለሙያዎችና በአፋርና ሶማሌ ክልሎች በመደባቸው አማካሪዎች አማካኝነት እስከ ወረዳና ት/ቤት የዘለቀ ሙያዊ ድጋፍ በመሰጠት ላይ ነው። በ1994 ዓ.ም በአፋርና ሶማሌ ክልሎች በአማካይ 12.9% የነበረው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ በ5 ዓመት ውስጥ በአማካኝ ወደ 29.5% ማደጉ በመሰጠት ላይ ያለው ልዩ ድጋፍ





በክልሎቹ የትምህርት እንቅስቃሴ ላይ ተጨባጭ ለውጥ እያመጣ መሆኑን ያመለክታል።

በተመሳሳይ በኦሮሚያና በደ/ብ/ብ/ሕ ክልሎች የተቋቋሙ የአርብቶ አደር ልማት ኮሚሽኖችና የክልሎቹ ትምህርት ቢሮዎች በየክልላቸው የሚገኙ አርብቶ አደር ወረዳዎችን የትምህርት አገልግሎት ለማሳደግ የተቀናጀና ውጤታማ የሆነ ሥራ በማከናወን ላይ ናቸው።

ከዚህም በተጨማሪ በርካታ ዓለም አቀፍና አገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች መንግሥት በአርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚያካሂዳቸው መደበኛና አማራጭ የትምህርት ፕሮግራሞች የገንዘብ፣ የቁሳቁስና የቴክኒክ ድጋፍ በመስጠት እንዲሁም ውስን በሆነ ደረጃም ቢሆን መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞችን በማካሄድ አበረታች አስተዋጽኦ በማበርከት ላይ መሆናቸው ሳይጠቀስ አይታለፍም።

## 3. የቁልፍ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦች ትርጉምና ማብራሪያ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የተካተቱ ቁልፍ ቃላትና ጽንሰ ሀሳቦች በመመሪያው ውስጥ ባላቸው አግባብና አጠቃቀም መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ተተርጎመውና ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

### 3.1 አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት

በአርብቶ አደሩ ሕብረተሰብ የኑሮ ሁኔታ ምክንያት በመደበኛ ት/ቤት ሊስተናገዱ ላልቻሉ ሕፃናት ከመደበኛው የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሣይክል (ከ፤ኛ - 4ኛ ክፍል) በአቻነት የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡ የትምህርቱ አሰጣጥ በባሕሪው ተለማጭ (flexible) እና ከአርብቶ አደሩ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ የተዘጋጀ ነው፡፡ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የአርብቶ አደሩን እንቅስቃሴ ሁኔታ መሠረት አድርጎ ከሚሰጥበት መንገድ አኳያ በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

#### 3.1.1 ቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት

አርብቶ አደሩ በቋሚ አሰፋፈር በሚኖርባቸው ወይም በአንድ ዓመት ውስጥ ቢያንስ ለ8 ተከታታይ ወራት በሚቆይባቸው አካባቢዎች በቋሚ የትምህርት መስጫ ማዕከል የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡

#### 3.1.2.ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት

አርብቶ አደሩ በአንድ ዓመት ውስጥ በአንድ ቦታ ላይ የሚያደርገው ቆይታ ከ8 ወራት በታች በሆነባቸው አካባቢዎች የትምህርት መስጫ ማዕከላትን፣ የትምህርት ቁሳቁሶችንና አመቻቾችን ከሕብረተሰቡ ጋር በማንቀሳቀስ የሚሰጥ ትምህርት ነው፡፡

### 3.2 አመቻቾች

ከአርብቶ አደሩ ማህበረሰብ ጋር ከቦታ ቦታ እየተንቀሳቀሱ የማስተማር አገልግሎት የሚሰጡ ከፊል ባለሙያዎች (Para-professionals) ናቸው፡፡

### 3.3 አሀዳዊ (self-contained) የማስተማር ዘዴ

አንድ /ዲት/ አመቻች በአንድ ዓይነት የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ይዞ/ ዛ/ በደረጃው የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶችን በሙሉ ብቻውን /ዋን የሚያስተምርበት /የምታስተምርበት/ ዘዴ ነው፡፡

### 3.4 አጣምሮ (Multi-grade) የማስተማር ዘዴ

አንድ /ዲት/አመቻች በተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች የሚገኙ ተማሪዎችን በአንድ መማሪያ ክፍል በተመሳሳይ ጊዜ ውስጥ የሚያስተምርበት /የምታስተምርበት/ዘዴ ነው።

### 3.5 ሽግግር (Transfer)

በተንቀሳቃሽና ቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት እንዲሁም በመደበኛው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞች መካከል በተመጣጠነ ደረጃ የሚፈፀም የተማሪዎች ሽግግር ወይም ዝውውር ነው፡፡

### 3.6 መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (NGOs)

በአርብቶ አደር አካባቢዎች ውስጥ በአጠቃላይ በአርብቶ አደሩ ትምህርት በተለይም በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የተሰማሩ ወይም ለፕሮግራሙ የፋይናንስ፣ የማቴሪያልና የቴክኒክ ድጋፍ የሚሰጡ አትራፊ ያልሆኑ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው፡፡





### 3.7 አጋርነት (Partnership)

የአርብቶ አደሩ ትምህርት ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከታቸው የፌዴራልና የክልል መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ህብረተሰቡና ሌሎችም ጉዳዩ የሚመለከታቸው ክፍሎች አቅማቸውን አስተባብረው የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የታለመለትን ግብ እንዲመታ በቅንጅት የሚሰሩበት ትስስር ነው፡፡

## 4. የተንቀሳቃሽ ትምህርት ባሕሪያትና የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች

- የአርብቶ አደሩ የኑሮ ሁኔታ ዋነኛ መገለጫ ለከብቶች ውሃና ግጦሽ ፍለጋ ከቦታ ቦታ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ነው። ነገር ግን የእንቅስቃሴው ድግግሞሽና ርዝማኔ ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡

- አርብቶ አደሩ በአንድ ቦታ ላይ 8 ወር እና ከዚያ በላይ የሚቆይ ከሆነ ቋሚ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን በአካባቢው በማቋቋም ትምህርት ይሰጣል፡፡ ነገር ግን አርብቶ አደሩ በአንድ ዓመት ውስጥ በአንድ ቦታ የሚቆየው ከ8 ወር በታች ከሆነ የተንቀሳቃሽ ትምህርት አገልግሎት መስጠት አስፈላጊ ይሆናል፡፡

- አርብቶ አደሩ በዓመት ውስጥ የሚንቀሳቀስበት ቦታና ጊዜ በውል የታወቀና በከፊል በቋሚ መንደሩና በከፊል ደግሞ ቆይታ የሚያደርግበት ቦታ የተወሰነ ከሆነ በቋሚ መንደሩ ቋሚ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያን በመጠቀም በሚንቀሳቀሱበት ቦታ ደግሞ ሣተላይት የትምህርት መስጫ ጣቢያ በመጠቀም የትምህርት አገለግሎት መስጠት ይቻላል፡፡

- አርብቶ አደሩ ከቦታ ቦታ የሚያደርገው እንቅስቃሴ በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይና ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ከሆነ የትምህርት አቅርቦት በዚያን መጠን ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

- ሌላው የፕሮግራሙ ዓይነተኛ ባሕሪ ለክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ አስቸጋሪ መሆኑ ነው፡፡

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው ዕድሜአቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱ መሆናቸው በውል ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡ የማይንቀሳቀሱ





ከሆነ በቋሚ የትምህርት አቅርቦት ስልቶች መጠቀም ይገባል፡፡

- የአንድ ጎሣ አባላት በቡድን ተከፋፍለው ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች የሚንቀሳቀሱ ከሆነ አመቻቹ/ቿ/፡-
  - ◊ በቁጥር አብላጫ ያላቸው ተማሪዎች የሚሄዱበትን ቡድን ተከትሎ /ላ/ መሄድ ይኖርበታል፡ /ይኖርባታል/።
  - ◊ ተማሪዎች እኩል በሆነ ቁጥር የሚከፈሉ ከሆነ አመቻቹ ጀማሪ የሆኑ ተማሪዎች ያሉበትን ቡድን ተከትሎ/ላ/ ይሄዳል/ትሄዳለች/
  - ◊ ከላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ከአመቻቻቸው የተለዩ ተማሪዎች በገፅ 23 ላይ በተጠቀሰው ሁኔታ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ሁኔታዎች ሲመቻቹ ተማሪዎች ከሌሎች ተማሪዎችና ከአመቻቻቸው ጋር ይቀላቀላሉ፡፡

- በአንድ አካባቢ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ከመጀመሩ በፊት የአርብቶ አደሩ የእንቅስቃሴ ሁኔታ፣ የእንቅስቃሴ ጊዜ፣ ቆይታ፣ ቦታ እና በእንቅስቃሴ የሚሳተፉ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ቁጥር ወዘተ የሚመለከት ትክክለኛና ዝርዝር መረጃ በወረዳ ትም/ጽ/ቤት ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ በመረጃ አሰባሰቡ ሂደት የወረዳ ትም/ጽ/ቤት ሌሎች ባለድርሻ አካላትን ያሳትፋል።

- የተንቀሳቃሽ ትምህርት ፕሮግራም ከመጀመሩ በፊት ሕዝቡ ይጠቅመኛል ብሎ እንዲቀበለውና ንቁ ተሣትፎ እንዲያደርግ በቂ የግንዛቤ ማዳበሪያና የአህዝቦት ሥራ በወረዳ ትም /ጽ/ቤት አስተባባሪነት መከናወን

ይኖርበታል፡፡

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም ከመጀመሩ በፊት የሚከተሉትን ነጥቦች በትኩረት ማጤን ይገባል፡፡
  - ◊ በቀላሉ ውጤት ሊገኝባቸው የሚችሉ አካባቢዎች (ለምሳሌ አመቻቾች በቀላሉ የሚገኙበት፣ በርካታ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ሕፃናት ያሉበት) ቅድሚያ መስጠት፣ በቀላሉ ሊደረስባቸው የማይችሉ አካባቢዎችን በቀጣይነት መስራት፣
  - ◊ ሕብረተሰቡ ትምህርቱን ለማስጀመር ያለው ፈቃደኝነትና ተሣትፎ ከፍተኛ ለሆነበት አካባቢ ቅድሚያ መስጠት፣
  - ◊ የአርብቶ አደሩ የእንቅስቃሴ ሁኔታ ያልተወሳሰበና በውል የሚታወቅ በሆነበት አካባቢ ትምህርቱን በቅድሚያ መጀመር፣

  - ◊ የመማር ማስተማሩ ሥራ በየወቅቱ እንዳይተጓጎል አመቻቾች ባሉበት ቦታ ደመወዛቸውን የሚያገኙበትን ስልት የወረዳ ትም/ጽ/ ቤቶች መቀየስ፤

- በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም በተቻለ መጠን ሴቶች ከወንዶች እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡ በሌላ አነጋገር በየትምህርት መስጫ ጣቢያው የሚኖረው የሴትና የወንድ ተማሪዎች ቁጥር የተመጣጠነ እንዲሆን ጥረት ይደረጋል።





- በየትምህርት መስጫ ጣቢያ በሚቋቋመው የትምህርት አመራር ኮሚቴ ውስጥ ሴቶች በአባልነት ይወከላሉ፡፡

- የተንቀሳቃሽ ትምህርት ኘሮግራም ከመጀመሩ በፊት ከኘሮግራሙ ተንቀሳቃሽ ባሕሪ ጋር ተስማሚ የሆኑ የመማሪያ ማስተማሪያ ቁሳቁሶችና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ሊሟሉ ይገባል፡፡ ከነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።
  - ◊ ተጣጣፊና በቀላሉ መንቀሳቀስ የሚችል ጥቁር ሰሌዳ፣
  - ◊ ተማሪዎች መልመጃዎችን የሚሰሩባቸው በነፍስ ወከፍ በእጅ የሚያዙ ጥቁር ሰሌዳዎች፣
  - ◊ አመቻቹና ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ቀለም ያላቸው ጠመኔዎችና ዳስተር፣
  - ◊ ለተማሪዎች መቀመጫነት የሚያገለግሉ በቀላል ዋጋ የሚገዙ ሰሌን፣ (ጋዴታ) ኘላስቲክ ምንጣፍ ወይም በቀላሉ ከቦታ ቦታ ሊጓጓዝ የሚችል ተጣጣፊ በርጩማ፣ወይም ከኘላስቲክ የተሰሩ ትንንሽ መቀመጫዎች፤
  - ◊ ለሳይንስና ሂሣብ ትምህርቶች የሚያገለግሉ የትምህርት መሣሪያዎችን የያዘ ኪት፣
  - ◊ የመማሪያ ማስተማሪያ መፅሐፍት
  - ◊ ልዩ ልዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችንና የተለያዩ የፅሕፈት መሣሪያዎችን ያካተተ ኪት (ሣጥን)፣
  - ◊ ሕፃናትና ጎልማሶች በማታም መማር እንዲችሉና አመቻቾችም ለትምህርት ዝግጅታቸው በቂ ብርሃን እንዲያገኙ ማሾ ወይም

ሌሎች አማራጭ የብርሃን ምንጮች፣

◊ አመቻቾች ለትምህርት ዝግጅት በቂ ጊዜ እንዲያገኙና ከተማሪዎቻቸው እንዳይርቁ መጠነኛ ስፋት ያለው ድንኳን ወይም ከአካባቢ ቁሳቁስ በቀላሉ ሊሰራ የሚችል ተንቀሳቃሽ መኖሪያ ቤት፣

◊ የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ መስጫ ሳጥን (First aid kit)

◊ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ተማሪዎች በተለይም ሴት ተማሪዎች በመሠረታዊ የፅሕፈት መሣሪያዎች እጦት ምክንያት ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ የፅሕፈት መሣሪያዎችን ከባለድርሻዎች በሚገኝ ድጋፍ በነፃ ወይም በግዢ በቀላሉ የሚያገኙበትን ስልት መቀየስ ፡

- የተንቀሳቃሽ ትምህርት ፕሮግራም የበለጠ ውጤታማ እንዲሆን፡-

◊ ሕብረተሰቡ ልጆቹን በተለይም ሴት ልጆቹን ወደ ትም/ቤት እንዲልክ መቀስቀስ፣

◊ በትምህርት ፕሮግራሙ አመራር ላይ በንቃት እንዲሳተፍ ማድረግ፣

◊ ሕብረተሰቡን በማስተባበር የትም/ሥራ እንዲጎለብት ማድረግ፣

◊ ለትምህርቱ ሥራ በጉልበታቸው፣ በገንዘባቸውና በእውቀታቸው በመርዳት ወዘተ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ላበረከቱ ግለሰቦችና ባለሙያዎች የማበረታቻ ሽልማቶችን መስጠት፣

◊ በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት ያገኙ ተማሪዎችን እንዲሁም ለፕሮግራሙ ስኬት አርአያነት ያለው ሥራ ያከናወኑ አመቻቾችን





በየዓመቱ መሸለም ያስፈልጋል፤

## 5. የመመሪያው ዓላማዎች

የዚህ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም አተገባበር መመሪያ ዋና ዓላማ ጥራት ያለው ትምህርት ወጥነት ባለው መልኩ በአርብቶ አደር አካባቢዎች እንዲተገበር ማድረግ ነው። ዝርዝር ዓላማዎቹም የሚከተሉት ናቸው።

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ከመደበኛው ትምህርት ጋር ያለውን አቻነትና ጥራት መጠበቅ፣
- በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የተሰማሩ አካላትን የተዘበራረቀ አሰራር በማስቀረት ወጥነት ያለው የአመራርና አተገባበር ሥርዓት ማስፈን፣

## 6. የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት

### 6.1. መርሀ ትምህርት፣ የትምህርት ደረጃና የትምህርት ዓይነቶች

#### 6.1.1. መርሀ ትምህርት

በመሠረቱ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት የአርብቶ አደሩን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት አድርጎ የተዘጋጀው የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ነው፡፡ ይህም የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት በመደበኛው የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሣይክል (1-4) ሥርዓተ ትምህርት ላይ ተመስርቶ በአቻነት የተዘጋጀ ነው፡፡ ስለሆነም የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ከመደበኛው ትምህርት የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሣይክል ጋር አቻነት ይኖረዋል፡፡ ይህም ማለት በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ ያጠናቀቁ ተማሪዎች በመደበኛው ትምህርት አምስተኛ ክፍል ገብተው ትምህርታቸውን መቀጠል ይችላሉ፡፡





የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት የቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መሠረታዊ ይዘቶችን ሳይለቅ የየአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ በማገናዘብ አካባቢያዊ (localize) ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

#### 6.1.2 የትምህርት ደረጃና ትምህርት የማጠናቀቂያ ጊዜ

እስካሁን ድረስ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት 4 ዓመት የሚወስደውን የመደበኛ መጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርትን በመጭመቅ በ3 ዓመት እንዲጠናቀቅ ሆኖ ሲሰጥ ቆይቷል። ለዚህም ምክንያቱ ፕሮግራሙ መጀመሪያ የተዘጋጀው የትምህርት ዕድል በማጣት ት/ቤት የመግቢያ እድሜያቸው ለተላለፉቸውና በእድሜ ትልቅ ለሆኑ ልጆችና ወጣቶች በመሆኑና እነዚህ ታዳሚያቸው ከእድሜ የገበዩትን እውቀት ግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ በመሆኑ ነው። ነገር ግን በጊዜ ሂደት አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት በተለይም በአርብቶ አደር አካባቢዎች ሕፃናት የሚስተናግዱበት ዋነኛ የትምህርት አቅርቦት ስልት እየሆነ በመምጣቱ በፕሮግራሙ ትምህርት ከሚጀመሩት አብዛኛዎቹ በመደበኛው የት/ቤት መግቢያ ዕድሜ የሚገኙ ልጆች ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ በእድሜ ትልቅ የሆኑ ልጆችና ወጣቶች ናቸው። ስለሆነም ትምህርት ሚኒስቴር የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ደረጃዎችንና የትምህርት ማጠናቀቂያ ጊዜን ከእነዚህ ሁለት ዓይነት ታዳሚዎች (Target groups) አኳያ መርምሮ ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት በቋሚም ሆነ በተንቀሳቃሽ ጣቢያዎች የሚሰጠው አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት፤

- በመደበኛው የት/ቤት መግቢያ ዕድሜ ትምህርት ለሚጀምሩ ልጆች በ4 ደረጃዎች ተከፍሎ በ4 ዓመት የሚጠናቀቅ ይሆናል።

- ዕድሜያቸው 10 ዓመትና በላይ ሆኖ ትምህርት ለሚጀምሩ ደግሞ በ3 ደረጃዎች ተከፍሎ በ3 ዓመት የሚጠናቀቅ ይሆናል።
- በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የሚታቀፉ ተማሪዎች የአንድ ደረጃን (ዓመትን) ትምህርት በአንድ ቦታ ተቀምጠው የሚያጠናቅቁበት ሁኔታ ባለመኖሩ የዓመቱን ትምህርት በንዑሳን ክፍሎች ከፋፍሎ መስጠት ተማሪዎቹ በአንድ ቦታ ቆይታቸው ቢያንስ አንድ ንዑስ ክፍል እንዲያጠናቅቁ ምቹ ሁኔታ ይፈጥርላቸዋል።

*ስለሆነም፡-*

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህረትን በመደበኛው የት/ቤት መግቢያ እድሜ (7-10ዓመት) ለሚጀምሩ ተማሪዎች የየደረጃው (የዓመቱ) ትምህርት በ3 ንዑሳን ክፍሎች፣ የ4ቱ ደረጃዎች ትምህርትም በ12 ንዑሳን ክፍሎች ተከፍሎ ይሰጣል፤
- ዕድሜያቸው ከ11-14 ዓመት የሆኑ ተማሪዎች ደግሞ በአንድ ዓመት ውስጥ 4 ንዑሳን የትምህርት ክፍሎችን እየተማሩ የ4ቱን ዓመት ትምህርት በ3 ዓመት እንዲያጠናቅቁ የሚደረግ ሲሆን አፈፃፀሙም ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።





### 6.1.3 የትምህርት ዓይነቶች

በተንቀሳቃሽ ትምህርት በዋነኛነት የሚሰጡ የትምህርት ዓይነቶች የአካባቢው አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ሂሣብ፣ እንግሊዝኛና አካባቢ ሣይንስ ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ እንደ ክልሎች ተጨባጭ ሁኔታ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን፣ በዕድሜ ትልቅ ለሆኑ ተማሪዎች ከደረጃ ሁለት ጀምሮ፣ ለሌሎች ተማሪዎች ደግሞ ከደረጃ ሶስት ጀምሮ ይሰጣል።

- አንደኛ ዓመት → የደረጃ አንድን ክፍል 1፣2 እና 3; የደረጃ ሁለትን ክፍል 1
- ሁለተኛ ዓመት → የደረጃ ሁለትን ክፍል 2 እና 3; የደረጃ ሶስትን ክፍል 1 እና 2
- ሶስተኛ ዓመት → የደረጃ ሶስትን ክፍል 3; የደረጃ አራትን ክፍል 1፣ 2 እና 3

በዋነኛነት ያልተካተቱት እንደ ስዕል ሙዚቃና የሰውነት ማጎልመሻ የመሳሰሉት የትምህርት ዓይነቶች ከፍ ብሎ በዋነኛነት ከተጠቀሱ የትምህርት ዓይነቶች ጋር ተቀናጅተው ይሰጣሉ:: ለምሳሌ የሙዚቃ ትምህርትን ከሂሣብና ከቋንቋ ትምህርት ጋር አዛምዶ ማስተማር ይቻላል::

## 6.2 የመማሪያ ማስተማሪያ መፅሐፍት

- ለተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት በመማሪያ ማስተማሪያነት የሚያገለግሉ መጻሕፍት በሞጁል መልክ የሚዘጋጁ ሲሆን በየደረጃው በ3 ንዑሳን ክፍሎች ተከፍሎ የሚሰጠው እያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት 3 ሞጁሎች ይኖሩታል። የሚዘጋጁት ሞጁሎች የሚከተሉትን አበይት ባህሪያት እንዲኖራቸው ይጠበቃል፡፡

  ◊ ተማሪው በቀላሉ አንብቦ ሊረዳው በሚችል ቋንቋ የተዘጋጁ፣
  ◊ ለመያዝና ለመጠቀም አመቺ እንዲሁም ማራኪ የሆኑ ፣
  ◊ በቂ የሥዕል መግለጫዎች ያላቸው፣
  ◊ ከሕፃናቱ ችሎታና በደረጃው ከሚሰጠው ትምህርት ጋር የሚመጣጠኑ መልመጃዎችንና ተግባራትን (Activities) ያካተቱ፣
  ◊ ተማሪዎች ያለ አስተማሪ እርስ በርስም ሆነ በግል ሊማሩበት በሚያስችል መልኩ የተዘጋጁ፣
  ◊ የግልና የቡድን ሥራዎችን የሚያበረታቱና ለተግባራዊ መልመጃዎች በቂ ትኩረት የሚሰጡ፣

- ሞጁሎች ተዘጋጅተው ሥራ ላይ እስኪውሉ ድረስ ለቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ተዘጋጅተው አገልግሎት በመሰጠት ላይ የሚገኙ የመማሪያ-ማስተማሪያ መፃሕፍት ለተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትም እንዲያገለግሉ ይደረጋል።





- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች በተቻለ መጠን የሚከተሉትን መሠረታዊ የትምህርት ቁሳቁሶች አሟልተው መገኘት ይጠበቅባቸዋል።

  ◊ በክልል ደረጃ በየትምህርት ዓይነቱ እና ደረጃው የተዘጋጀ መርሃ ትምህርት (ሲለበስ)፣
  ◊ በየደረጃውና በየትምህርት ዓይነቱ የተዘጋጁ የአመቻቾች መመሪያ እና የተማሪዎች መማሪያ መፅሐፍት፣
  ◊ አመቻቾችና ተማሪዎች የሚጠቀሙባቸው ተጨማሪ የንባብ ፅሁፎች፣
  ◊ በተለያዩ ማህበራዊና አንገብጋቢ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ልዩ ልዩ ፖስተሮች ለምሳሌ ስለ HIV/AIDS፣ የሴት ልጅ ግርዛት እና አካባቢ ጥበቃ ወዘተ ግንዛቤ የሚያስጨብጡ ስዕላዊ መግለጫዎችና ፖስተሮች፣
  ◊ የተማሪዎች ሪከርድ መያዣ ልዩ ልዩ ቅፃቅፆችና መዝገቦች፣
  ◊ የትምህርት እቅድ ዝግጅት ደብተሮች፣
  ◊ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም አተገባበር መመሪያ፣

## 6.3 የትምህርት መስጫ ቦታና ጊዜ

### 6.3.1. የትምህርት መስጫ ቦታ

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የሚሰጥበትን ቦታ

ሕብረተሰቡ በጋራ በመወያየት ይወሰናል። ትምህርቱ እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በዛፍ ጥላ ሥር፣ በዳስ ወይም በተንቀሳቃሽ ድንኳን ሊሰጥ ይችላል፣

- ትምህርቱ በድንኳን ውስጥ የሚሰጥ ከሆነ ድንኳኑ በቀላሉ ከቦታ ቦታ ሊጓጓዝና ሊገጣጠም የሚችል፣ በቂ አየር የሚያስገባና የአካባቢውን የአየር ሁኔታ ያገናዘበ፣ ቀለሙም ከአካባቢው ቶፖግራፊ ጋር ተገናዝቦ የተዘጋጀ የተማሪውን ደህንነት በአስተማማኝ መጠበቅ የሚያስችል (ለአደጋ ያልተጋለጠ) መሆን ይኖርበታል።

- ለትምህርት መስጫ የሚዘጋጁ ድንኳኖች በመጠነኛ ወጪ አገር ውስጥ የሚመረቱ፣ ከ30-35 ተማሪዎችን መያዝ የሚችሉና በአማካይ 25 ካሬ ሜትር ስፋት ያላቸው መሆን አለባቸው።
- ትምህርቱ በዳስ የሚሰጥ ከሆነ የዳሱ አሰራር በቂ ተማሪዎች መያዝ የሚችል፣ የሚሰራበት ማቴሪያልና አሰራሩም በተማሪዎች ላይ አደጋ የማያስከትል መሆን ይኖርበታል።
- በትምህርት መስጫ ጣቢያ አካባቢ ለህፃናቱ በቂ የመጫወቻ ሥፍራና ቁሳቁስ ሊኖር ይገባል።
- በትምህርት መስጫ ቦታ ህፃናት በውሃ አጋር የታከመና ጤንነቱ የተጠበቀ የውሃ አገልግሎት ሊያገኙ ይገባል። ይህም ህፃናቱ ወደ ት/ቤት እንዲመጡ ከሚያደርጋቸው ምክንያቶች አንዱ ነው።

### 6.3.2. የትምህርት መስጫ ጊዜ

- የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጊዜ





በሕብረተሰቡና በአመቻቹ በጋራ በመመካከር የሚወሰን ሆኖ በተቻለ መጠን ተማሪዎች ለቤተሰቦቻቸው የሚሰጡትን እገዛ በማይጋፋ (በማያስተጓጉል) መልኩ መሆን ይኖርበታል።

- የትምህርት መስጫ ጊዜና ቦታ የሕብረተሰቡን አኗኗር፣ የሥራ ሁኔታ፣ የአየር ንብረት ወዘተ ግምት ውስጥ ያስገባና የተጠቃሚውን ማህብረሰብ ይሁንታ (ተቀባይነት) ያገኘ መሆን ይኖርበታል። ለምሳሌ ያህል የዕለቱን ትምህርት በሙሉ በአንድ ፈረቃ መስጠት ተማሪው ወላጆቹ ከሚሰጠው የጉልበት (የሥራ) አገልግሎት ጋር የማይጣጣም ሆኖ ቢገኝ ከፊሉን ትምህርት ጠዋት፣ ቀሪው ትምህርት ደግሞ ከሰዓት በኋላ ወይም ማታ መስጠት ይቻላል።

- በአንድ ዓመት ውስጥ ከ203-206 የትምህርት ቀናት ይኖራሉ።
- ተማሪዎች በዓመት ውስጥ ከእንቅስቃሴ ውጪ በሚሆኑባቸው ጊዜያት ሁሉ በሣምንት ስድስት ቀናት በቀን አራት ባለ 40 ደቂቃ ክፍለ ጊዜያትን በድምሩ 6 ቀን x 4 ፔሬድ x 40 ደቂቃ = 960 ደቂቃ ወይም 16 ሰዓት ትምህርት ይከታተላሉ።

- የትምህርት መስጫ ጊዜን ተጠቃሚ ማህበረሰብ ይወስናል ሲባል በአንድ የትምህርት ቀን መሸፈን ያለበት የ4 ፔሬድ ወይም የ160 ደቂቃ ትምህርት እና በአንድ ሳምንት 6 የትምህርት ቀናት መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የቀኑ ትምህርት መቼ እንደሚሰጥ /ጥዋት፣ ከሰዓት በኋላ፣ ማታ/ እና የሳምንቱ የትምህርት ቀናት እነማን እንደሆኑ /ምሳሌ፣ ሰኞ፣ማክሰኞ፣ ረቡዕ፣ሀሙስ፣ ቅዳሜ፣ እሁድ/ ይወሰናል ማለት እንደሆነ ግንዛቤ ሊወሰድ ይገባል።

- የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ተማሪዎች ትምህርታቸውን በራሳቸው የትምህርት አቀባበል ችሎታና ፍጥነት የሚማሩ ቢሆንም በየደረጃው ለሚሰጥ መርሃ ትምህርት የተመደበው የክፍለ ጊዜ ብዛትና ትምህርት ሙሉ በሙሉ መሸፈን ይኖርበታል፡፡

- ለእያንዳንዱ የትምህርት ዓይነት የሚመደበው ክፍለ ጊዜ ከሚሰጠው የትምህርት ዓይነት ይዘት እና በመደበኛው ትምህርት ፕሮግራም ለትምህርቱ ከተሰጠው ክፍለ ጊዜ ጋር የተጣጣመ ይሆናል፡፡ በዚህም መሠረት ለእያንዳንዱ ደረጃና የትምህርት ዓይነት የተመደበው ሳምንታዊ ክፍለ ጊዜ ሥርጭት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**<u>የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት</u>**

**<u>ሳምንታዊ የክፍለጊዜ ስርጭት ሰሌዳ</u>**

***ሀ. ፕሮግራሙን በ4 ዓመት ለሚያጠናቅቁ ተማሪዎች***





| ደረጃ | የትምህርት ዓይነት | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አፍ መፍቻ ቋንቋ | እንግሊዝኛ | ሂሣብ | አካባቢ ሣይንስ | አማርኛ | |
| I | 5 | 6 | 6 | 7 | - | 24 |
| II | 5 | 6 | 6 | 7 | - | 24 |
| III | 4 | 5 | 6 | 6 | 3 | 24 |
| IV | 4 | 5 | 6 | 6 | 3 | 24 |
| ድምር | 18 | 22 | 24 | 26 | 6 | 96 |

**ለ. ፕሮግራሙን በ3 ዓመት ለሚያጠናቅቁ ተማሪዎች**

| ደረጃ | የትምህርት ዓይነት | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | አፍ መፍቻ ቋንቋ | እንግሊዝኛ | ሂሣብ | አካባቢ ሣይንስ | አማርኛ | |
| I | 5 | 6 | 6 | 7 | - | 24 |
| II | 4 | 5 | 6 | 6 | 3 | 24 |
| III | 4 | 5 | 6 | 6 | 3 | 24 |
| ድምር | 13 | 16 | 18 | 19 | 6 | 72 |

- ከአቅም በላይ በሆነ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ምክንያት ሕብረተሰቡ ለረጅም ጊዜ ሊበታተንና የመማር ማስተማሩ ሥራ ሊቋረጥ ይችላል፡፡ ሕብረሰቡ ወደ ቦታው ሲመለስና ሁኔታዎች ሲረጋጉ የተቋረጠው ትምህርት ከቆመበት ቦታ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ ለዚህም አመቻቾች ከወረዳ ትም/ጽ/ቤትና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን አስፈላጊውን መረጃ መያዝ አለባቸው።

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች ለማህበረሰቡ ቅርብ የሆኑ ማዕከላት ናቸው፡፡ ስለሆነም ለልጆች ከሚሰጡት የትምህርት አገልግሎት በተጨማሪ ማህበረሰቡን በተለያዩ አካባቢያዊ የጤና፣ የእንስሳት እርባታ፣ ወዘተ ችግሮች ላይ ለማወያየትና የጋራ መፍትሄ ለመፈለግ እንዲሁም ከዕለት ተዕለት ኑሮና መተዳደሪያ ጋር የተዛመደ ተግባር-ተኮር ትምህርት ለጎልማሳ አርብቶ አደሮች ለመስጠት የሚያስችሉ ጠቃሚ ማዕከላት መሆናቸውን በመገንዘብ የአገልግሎት አድማሳቸውን ማስፋት ያስፈልጋል፡፡

### 6.4 የትምህርቱ አቀራረብ

በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ዋናዎቹ ተዋናዮች ተማሪዎች ናቸው፡፡ የአመቻቾች ሚና ተማሪዎች በራሳቸው አቅም እንዲማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸትና እንደ ትምህርት አቀባበላቸው ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪ ተኮርና በተግባር ላይ የተመሠረተ እውቀትና





ክህሎትን በማስጨበጥ የተማሪዎችን የችግር ፈቺነት አቅም በሚያጎለብቱ ዘዴዎች ላይ መመስረት ይኖርበታል፡፡

- በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት የመማር ማስተማር ሥራ እንደ መደበኛውና ቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት በአንድ አመቻች የሚከናወን በመሆኑ አህዳዊ የማስተማር ዘዴን (self contained) የሚከተል ይሆናል፡፡

- በአንድ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ በየደረጃው የሚኖሩ ተማሪዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ ሆኖ ሲገኝ አመቻቾች አጣምሮ የማስተማር ዘዴን (multi grade approach) ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

- ከፍ ብሎ በተጠቀሱት ምክንያቶች አመቻቾች በአሀዳዊ እና በአጣምሮ የማስተማር ዘዴዎች ላይ በቂ የቅድመ ሥራ እና የሥራ ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

- ከመማሪያ ማስተማሪያ መፅሐፍት በተጨማሪ አመቻቾች ተማሪዎችን በማሳተፍ የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን በአካባቢው ከሚገኙ ቁሳቁሶች እያዘጋጁ ሥራ ላይ በማዋል የመማር ማስተማሩን ሂደት ያጠናክራሉ፡፡

- በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የሚሰጠው የገፅ ለገፅ ትምህርት በትምህርት በሬዲዮ ፕሮግራም ይደገፋል፡፡ ተማሪዎች ያለ አመቻች በሚቆዩባቸው ወቅቶችና የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ሲሆን በክልል ደረጃ የትምህርት ፕሮግራሞችን በካሴት በማባዛት ከቴፕ ሪኮርደር ጋር ለአመቻቾች በኃላፊነት ተሰጥቶ ጥቅም ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

- በተለያዩ አቅጣጫዎች ተንቀሳቅሰው የነበሩ ተማሪዎች እንደገና በሚገናኙበት ወቅት አመቻቾች ወደኋላ ለቀሩ ተማሪዎች ማካካሻ በመስጠት ሁሉም ተማሪዎች ወደ ተመሳሳይ ምዕራፍና ይዘት እንዲመጡ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

- በአንድ ዓይነት የትምህርት ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎችን በተመለከተም አመቻቾች ደካማና ጎበዝ ተማሪዎችን ቀላቅሎ በማስቀመጥ እርስ በእርሳቸው እንዲማማሩ ሁኔታዎችን የማመቻቸት፣ በትምህርታቸው ደከም ለሚሉትም እራሳቸው ልዩ ድጋፍ በመስጠት ውጤታማ እንዲሆኑ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

## 6.5 ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ያጠናቀቁ ተማሪዎች የሚኖራቸው የባሕሪ ገፅታዎች (Profile)

- በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የሚሰጠውን





ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች የሚከተሉትን የባሕሪ ገፅታዎች ይላበሳሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ እነዚህ ባሕሪያት ለመደበኛና ለቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ከተቀመጡት ባህሪያት ጋር ተመሳሳይነት (አቻነት) አላቸው፡፡

- የክፍል ደረጃውን የሚመጥን የእጅ ፅሁፍ የማንበብና የመሠረታዊ ስሌት ችሎታ አላቸው፡፡

- ስለራሳቸው ማንነትና ምንነት፣ ስለቤተሰባቸውና ሕብረተሰብ ኃላፊነቶችና ችግሮች መጠነኛ ግንዛቤ ይኖራቸዋል፡፡ አቅማቸው በፈቀደ መጠን ኃላፊነት ይሰማቸዋል፣ ችግሮችንም ለመፍታት ይሞክራሉ፡፡

- ልዩ ልዩ የቤት ውስጥ ቁሳቁሶችን ምንነት ጠቃሚነትና እንክብካቤ ያውቃሉ፣ በተግባር ይገልፃሉ፤ ያሳያሉ፡፡

- በአካባቢው ያሉትን የሥራና የምርት እንቅስቃሴዎች ያስተውላሉ ይገነዘባሉ፤ በሚፈልጓቸው የሥራ ዘርፎች ይሳተፋሉ፡፡

- በግለሰብ፤ በቤተሰብና በሕብረተሰብ ደረጃ እምነቶችን፣ አስተሳሰቦችንና ድርጊቶችን ይመረምራሉ፣ ያነፃራሉ፣ ይመርጣሉ፡፡

- አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ለመጠየቅና ለመረዳት

ይፈልጋሉ፤ ባገኙት ምክር ለመጠቀም ይጣጣራሉ፡፡

- ከችሎታቸውና ከአቅማቸው ጋር የሚጣጣሙ ልዩ ልዩ ሥራዎችን የመሞከርና የመለማመድ ከፍተኛ ፍላጎት ያሳያሉ፡፡

የግልና የአካባቢ ንፅህናቸውን ይጠብቃሉ፡፡

- ተግባርን በተናጠል ከመፈፀም ፈንታ እንደተገቢነቱ በጋራ ከንዋኔ ለጋራ ውጤት የመሰለፍ ስልትን ተለማምደዋል፡፡

## 6.6 የተማሪዎች ምዘናና ሽግግር

### 6.6.1. የተማሪዎች ምዘና

- በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የታቀፉ ተማሪዎች የሚመዘኑት በተከታታይ የምዘና ዘዴ (Continuous Assessment) ሲሆን ምዘናው ለየትምህርት ዓይነቱ በተቀረፀው መርሃ ትምህርት እያንዳንዱ ምዕራፍ ላይ በተቀመጡት የመመዘኛ መስፈርቶች እና በየጊዜው በሚሰጡ ተጨማሪ መመዘኛዎች አማካይነት በአመቻቾች ይከናወናል፡፡

- የተከታታይ ምዘናው ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን የነፍስ ወከፍና የቡድን ትምህርት አቀባበል በየወቅቱ በመገምገም ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ በመሆኑም አመቻቾች ከተከታታይ ምዘናዎች የሚያገ˜ቸውን ግብረ መልሶች (feed backs)መሠረት በማድረግ፡-





◊ ከፊሉ ወይም ብዙሃኑ ተማሪዎች በሚገባ ያልተረዷቸውን የትምህርት ይዘቶች የተሻሉ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎችን በመጠቀም ደግመው ያስረዳሉ፡፡

◊ ጎበዝ ተማሪዎች በትምህርታቸው የበለጠ እንዲተጉ ማበረታቻዎችንና ተጨማሪ ሥራዎችን ይሰጣሉ፤ ሌሎች ተማሪዎችን እንዲያስጠኑም ያበረታታሉ።

◊ ውጤታቸው ዝቅተኛ ለሆነ ተማሪዎች በግልና በቡድን ተጨማሪ ድጋፍ በመስጠት ወደሚቀጥለው የትምህርት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ያደርጋሉ፡፡

◊ የተማሪዎችን የተከታታይ ምዘና ውጤቶች በአግባቡ መዝግቦ በመያዝ ተማሪዎች በየወቅቱ የሚያሳዩትን መሻሻል ወይም የውጤት ማነስ ይከታተሉበታል፡፡ አስፈላጊውን የማሻሻያ እርምጃ ለመውሰድም ይጠቀሙበታል፡፡

- በትምህርት አሰጣጡ ተንቀሳቃሽ ባሕሪ ምክንያት ተማሪዎች ቀደም ሲል ከሚያስተምራቸው /ከምታስተምራቸው/ አመቻች ተለይተው ወደ ተለያዩ አቅጣጫዎች ከቤተሰቦቻቸው ጋር በሚንቀሳቀሱበት ወቅት አመቻቹ /ቿ/ ተማሪዎች ያጠናቀቁትን ትምህርትና የተከታታይ ምዘና ውጤት አጠናቅሮ /ራ/ እንቅስቃሴውን በበላይነት በሚመራው የጎሳ አባል

አማካይነት ትምህርት ለሚቀጥሉበት ጣቢያ አመቻች እንዲደርስ ያደርጋል (ታደርጋለች)።

- ተማሪዎች ከአንዱ ደረጃ ወደ ሚቀጥለው የሚሸጋገሩት በተከታታይ ምዘናዎች አማካይነት ለደረጃው የተመደበውን ትምህርት በሚገባ ማጠናቀቃቸው በአመቻቹ (ቿ) ሲያረጋግጥ ነው፡፡

- በየደረጃው መጨረሻ ተማሪዎች በየትምህርት ዓይነቱ ያገኙትን ውጤት የሚገልጽ ሪፖርት ካርድ ይሰጣቸዋል።

## 6.6.2. የተማሪዎች ሽግግር

በመደበኛ፣ በቋሚና ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞች የታቀፉ ተማሪዎች ትምህርታቸውን በጀመሩት ፕሮግራም እንዲያጠናቅቁ ማድረግ ይመረጣል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ ተማሪዎች በተለየዩ ምክንያቶች ባንደኛው ፕሮግራም የጀመሩትን ትምህርት በሌላው ፕሮግራም ለመቀጠል ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በዚህን ጊዜ የተማሪዎቹ የዝውውር ጥያቄ ከዚህ እንደሚከተለው ምላሽ የሚያገኝ ይሆናል።

በመደበኛው ትምህርት እንዲሁም በ4 ዓመቱ ቋሚና ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞች የታቀፉ ተማሪዎች ዝውውር ጥያቄ ሕጋዊ የትምህርት ማስረጃ በማቅረብ አቻነት ባለው ደረጃ ይፈፀማል። ለምሳሌ ያህል በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የደረጃ አንድን





ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች በደረጃ አንድ በተከታተሏቸው የትምህርት ዓይነቶች ያገኙትን ውጤት (ማርክ) የሚገልጽ፣ ወደ ደረጃ ሁለት መዛወራቸውን የሚያረጋግጥ፣ የቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ ወይም የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊ ፊርማና ማህተም ያለው ሕጋዊ የትምህርት ማስረጃ በማቅረብ በቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ በደረጃ ሁለት ወይም በመደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት በ2ኛ ክፍል ተመዝግበው ትምህርታቸው መቀጠል ይችላሉ። በተመሳሳይ በመደበኛ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት አንደኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ተማሪዎች ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች የሚያሟላ ሕጋዊ የትምህርት ማስረጃ በማቅረብ በቋሚ ወይም በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት በደረጃ ሁለት ተመዝግበው ትምህርታቸው መቀጠል ይችላሉ።

በ3 ዓመቱ የቋሚና ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የታቀፉ ተማሪዎችን በተመለከተ፡-

◊ የዝውውር ጥያቄው ከቋሚ ወደ ተንቀሳቃሽ ወይም ከተንቀሳቃሽ ወደ ቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ከሆነ አስፈላጊውን ሕጋዊ የትምህርት ማስረጃ በማቅረብ አቻነት ባለው ደረጃ ተፈፃሚ ይሆናል።

◊ የዝውውር ጥያቄው ከቋሚ ወይም ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ወደ መደበኛ መጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ከሆነ ደረጃ አንድን አጠናቅቀው ወደ ደረጃ ሁለት የተዛወሩ ተማሪዎች በመደበኛ ት/ቤት 2ኛ ክፍል፣ ደረጃ ሁለትን አጠናቀው ወደ ደረጃ ሶስት የተዛወሩ በመደበኛ ት/ቤት 3ኛ ክፍል ተመዝግበው ትምህርታቸውን መቀጠል ይችላሉ

◊ ደረጃ ሶስትን ያጠናቀቁ ተማሪዎች በመደበኛው ትምህርት 5ኛ

ክፍል ገብተው ትምህርታቸውን ይቀጥላሉ፤

በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም የሚሰጠውን ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች እንደ አመቺነቱ በመደበኛ ት/ቤት ወይም በአማካይ ቦታ በአነስተኛ ወጪና በህብረተሰብ ተሳትፎ በሚቋቋሙ አዳሪ ትም/ቤቶች ወይም በመደበኛ ትም/ቤቶች አቅራቢያ በሚሰሩ ሆስቴሎች እየኖሩ ከ5-8ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ይከታተላሉ።

## 7. የአመቻቾች ምልመላ፣ ሥልጠናና የሥራ ድርሻ

### 7.1 የአመቻቾች መመልመያ መስፈርቶችና የምልመላ አፈፃፀም፡-

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት በባህሪው አመቻቾች፣ ተማሪዎችና የትምህርት ቁሳቁሶች ከሕብረተሰቡ ጋር ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀሱበት የትምህርት አቅርቦት ስልት ነው፡፡ በመሆኑም





ለትምህርት ሥራ በአመቻችነት የሚመለመሉ ግለሰቦች ከሁሉም በፊት የማህበረሰቡ አባል የሆኑና ከሕብረተሰቡ ጋር ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ በአመቻችነት ለማገልገል ፍቃደኛ የሆኑ መሆን አለባቸው፡፡ በዚህም መሠረት አመቻቾች በሚከተሉት አበይት መስፈርቶች መሠረት ይመለመላሉ፡፡

- ◊ የአካባቢውን (የተጠቃሚውን ማህበረሰብ) ባሕልና ወግ የሚያውቁና የሚያከብሩ፣
- ◊ በአካባቢው ቋንቋ ማንበብና መፃፍ የሚችሉ፣
- ◊ የማስተማር አገልግሎት ለመስጠት ፍላጎት ያላቸው፣
- ◊ በሕብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው፣
- ◊ ኃላፊነትን ለመቀበል ብቁና ዝግጁ የሆኑ፣
- ◊ ቢያነስ የ8ኛ ክፍል ትምህርት ያጠናቀቁ፣
- ◊ ለሴት አመቻቾች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት በሚሰጥበት አካባቢ ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ የአካባቢው ተወላጆች ካልተገኙ ቋንቋውንና ባሕሉን የሚያውቁ፣ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሰው ለማስተማር ፍቃደኛ የሆኑና መስፈርቱን የሚያሟሉ ግለሰቦችን ከአጎራባች ቀበሌዎችና ወረዳዎች በአመቻችነት መመልመል ይቻላል፡፡

- የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም አመቻቾች የትምህርቱን ሥራ እንዲመራ ከተጠቃሚው ማህበረሰብ ተውጣጥቶ በተቋቋመው ኮሚቴ አማካይነት ከፍ ብሎ የተጠቀሱትን መስፈርቶች

መሠረት በማድረግ ይመለመላሉ፡፡ (ስለ ኮሚቴው አወቃቀርና የሥራ ድርሻ በክፍልII.1.5 ላይ ይመለከቱ) ፡፡ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ተወካይ ባለሙያ በቦታው በመገኘት ምልመላውን ያስተባብራል፡፡ የቴክኒክ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

- የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኮሚቴው መልምሎ ያቀረባቸው እጩ አመቻቾች በመመልመያ መስፈርት መሠረት መመረጣቸውንና ሕጋዊ የትምህርት ማስረጃ ማሟላታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ለሥልጠና ብቁ የሚያደርጋቸውን የመግቢያ ፈተና ይሰጣል፡፡ በውጤቱም መሠረት ተመልማዮችን ወደ ቅድመ ሥራ ሥልጠና ያስገባል፡፡

## 7.2 የአመቻቾች የቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ሥልጠናዎች

- የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም አመቻቾች አካባቢው ካፈራው የተማረ የሰው ኃይል የሚመለመሉ በመሆናቸው አብዛኛው ጊዜ የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም በፕሮግራሙ የሚሰጠውን ትምህርት ከመደበኛ ትምህርት ጋር አቻነት ያለውና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን የአመቻቾችን አካዳሚያዊና ሙያዊ ብቃት በተለያዩ መንገዶች እና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ መገንባት የማይታለፍ ተግባር ነው፡፡

- ለተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም አመቻቾች የሚሰጡ የቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ሥልጠናዎች ደረጃቸውን የጠበቁ ተከታታይነትና ወጥነት ያላቸው እንዲሆኑ ጉዳዩ በሚመለከታቸው





ክልል ት/ቢሮዎች አስተባባሪነት በተመረጡ መም/ትም/ኮሌጆች ውስጥ ተገቢው አደረጃጀት ተፈጥሮላቸው የሚከናወኑ ይሆናሉ፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተሉት የሥልጠና ዓይነቶች ለአመቻቾች ይሰጣሉ፡፡

### 7.2.1 የቅድመ ሥራ ሥልጠና፡-

- ለተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የተመለመሉ አመቻቾች ሥራ ከመጀመራቸው በፊት ለሶስት ተከታታይ ወራት የመነሻ ሥልጠና በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው፣ በአካባቢው የሥራ ቋንቋ ወይም በሚያስተምሩበት ቋንቋ ይወስዳሉ፡፡ በሥልጠናው የሚካተቱት አበይት ይዘቶች፡-
  - ◊ የተንቀሳቃሽ ትምህርት ምንነት፣ አስፈላጊነትና አበይት ባሕሪያት፣
  - ◊ የተንቀሳቃሽ ትምህርት አተገባበር፣
  - ◊ የማስተማር ሥነ ዘዴ ፣
  - ◊ አሀዳዊና አጣምሮ (multigrade) የማስተማር ዘዴዎች፣
  - ◊ ተከታታይ ምዘናና ግምገማ፣
  - ◊ የሕፃናት ሥነ ባሕሪ፣
  - ◊ አካቶ ትምህርት
  - ◊ የክፍል አያያዝ፣
  - ◊ የመረጃ አያያዝ
  - ◊ የትምህርት ዕቅድ ዝግጅት ወዘተ ይሆናሉ፡፡

- የአሰለጣጠኑ ስልትም የዕጩ አመቻቾችን አቅም ግምት ውስጥ ያስገባ በተጨባጭ ምሳሌዎች የታጀበና አመቻቾቹ ከሚያስተምሩት ትምህርት

ይዘት ጋር በቀጥታ የተገናኘ እንዲሁም ንድፈ ሀሳብን ከተግባር ጋር ያዛመደ ሊሆን ይገባል፡፡

- ለአመቻቾች ሥልጠና የሚያገለግሉ ሞጁሎች በክልል ትምህርት ቢሮዎች አስተባባሪነት በመም/ትም/ኮሌጆችና በክልሉ ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም በሚያካሂዱ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጋራ ይዘጋጃሉ። ትምህርት ሚኒስቴርም አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል።

**7.2.2 የሥራ ላይ ሥልጠና፡-**

- ለአመቻቾች የሚሰጡ የሥራ ላይ ሙያዊ ሥልጠናዎች በሱፐርቪዥን አማካይነት ተለይተው በታወቁ ሙያ ነክ ችግሮች፣ አሰልጣኝ ኮሌጆች ከድህረ ሥልጠና ግምገማ ባገኙቸው ግብረ መልሶች እና በአመቻቾች የሥልጠ ፍላጎቶች ላይ ተመስርተው ይዘጋጃሉ፡፡ ለሥራ ላይ ሥልጠናም እንደየሥልጠና ርዕሰ ጉዳዩ ተገቢ የሆነ የማሰልጠኛ ፅሁፎች ሥልጠናውን በሚሰጡ አካላት ይዘጋጃሉ፡፡

- አጫጭር የሥራ ላይ ሥልጠናዎች በክልል ትም/ቢሮዎች አስተባባሪነት በወረዳ ትም/ጽ/ቤቶች በኩል በተመረጡ ማዕከላት ይሰጣል፡፡ የወረዳ ትም/ጽ/ቤቶች ሥልጠናውን ለመስጠት በአካባቢው ከሚገኙ መደበኛ ትም/ቤቶች፣ በትምህርት ዘርፍ ከተሰማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባለሙያዎች እንዲሁም ከክልሉ ትም/ቢሮ የባለሙያ ድጋፍ መጠየቅ ይችላሉ፡፡





- ለአመቻቾች የሚሰጡ የሥራ ላይ ሥልጠናዎች በዓመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ በየሥልጠና ወቅቱ ለተከታታይ 3-5 ቀናት ይካሄዳሉ፡፡

- ለአመቻቾች ከሚሰጡ የቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ሥልጠናዎች በተጨማሪ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም አመቻቾች በአመት ቢያንስ ሁለት ጊዜ ለሁለት ቀናት በወረዳ ደረጃ ተሰባስበው እርስ በርስ የሚማማሩበትና መልካም ተሞክሮዎችን የሚለዋወጡበት እንዲሁም በመማር ማስተማሩ ሂደት የገጠሟቸውን አበይት ችግር በጋራ የሚፈቱበት መድረክ በወረዳ ትም/ጽ/ቤት አስተባባሪነት ይዘጋጃል፡፡ በሥልጠና በምክክር ስብሰባዎች ምክንያት የትምህርት ጊዜ እንዳይባክን ይህን የምክክር መድረክ በዓመት ሁለት ጊዜ ከሚሰጠው የሥራ ላይ ሥልጠና እና ጋር በአንድ ላይ አቀናጅቶ ማካሄድ ይቻላል።

- በቅድመ ሥራና የሥራ ላይ ሥልጠናዎች ለሚሳተፉ አመቻቾች የተሣትፎ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡ በየወቅቱ የተሰጡ ሥልጠናዎች መረጃዎች በአግባቡ ተጠናቅረው በወረዳና በክልል ደረጃ ይቀመጣሉ፡፡ እንደአስፈላጊነቱም ለቀጣይ ሥልጠናዎች በግብዓትነት ያገለግላሉ፡፡

**7.2.3 የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ሥልጠና፡-**

- በተመረጡ መም/ትም/ኮሌጆች ውስጥ በሚፈጠር የርቀት ትምህርት አደረጃጀት የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አመቻቾች

የትምህርት ደረጃቸውን በየጊዜው እያሻሻሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ ይደረጋል፡፡ ይህ ሁኔታ እስከሚፈጠር እንደአመቺነቱ የግል የርቀት ትምህርት ተቋማትን መጠቀም ይቻላል፡፡ ለዚህ የሚያስፈልገውን ወጪና ሌሎች ድጋፎች መንግሥት ይሸፍናል።

- በተለያየ መንገድ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁ አመቻቾች በመም/ትም ኮሌጆች በሚሰጥ የ2 ዓመት ተከታታይ የክረምት የገጽ ለገጽና የበጋ የርቀት ትምህርት ሥልጠና በሠርተፍኬት እንዲመረቁና መደበኛ መምህር እንደሆኑ ይደረጋል፡፡

## 7.3 የአመቻቾች የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

ለተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም ውጤታማነት ወሳኝ ሚና ከሚጫወቱ ኃይሎች መካከል ግንባር ቀደሞቹ አመቻቾች ናቸው፡፡ ስለሆነም በትምህርቱ ሥራ ላይ የሚከተሉት የሥራ ድርሻዎችና ኃላፊነቶች ይኖራቸዋል፡፡

- የየደረጃውን ተማሪዎች በሥም፣ በፆታና በዕድሜ በአግባቡ መዝግቦ መያዝና ወቅታዊ ማድረግ፣ ከወረዳ ት/ጽ/ቤት በሚላኩ ቅጾች የተማሪዎችን መረጃዎች በጥንቃቄ ሞልቶ ለጽ/ቤቱ በወቅቱ መላክ፣

- በየትምህርት ዕለቱ የተማሪዎች የሥም ቁጥጥር ማድረግ፣ በተደጋጋሚ የሚቀሩና ያቋረጡ ተማሪዎችን ዝርዝር ለጣቢያው ትምህርት አመራር ኮሚቴ ሪፖርት ማድረግና ከኮሚቴው ጋር በጋራ የተማሪዎቹን ወላጆች በማነጋገር ተማሪዎቹ ከትምህርት ገበታቸው እንዳይቀሩ ያቋረጡም





እንዲመለሱ ማድረግ፣

- የሚያስተምሯቸውን ተማሪዎች እንደወላጅ በፍቅር መንከባከብ፣
- ትምህርቱን ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ሳቢ፣ ማራኪና በተግባር የተደገፈ ማድረግ፣
- የሚሰጡ ትምህርቶችን ተማሪ ተኮር ማድረግና ሕፃናትን አሳታፊ የሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ማቅረብ፣

- ተማሪዎቻቸውን በስም፣ በሥነ-ምግባርና በትምህርት አቀባበል ችሎታቸው በመለየት አስፈላጊውን እገዛ ማድረግ፣

- በየወቅቱ በመርሃ ትምህርቱ ላይ በመመስረትና የተለያዩ የፈጠራ ዘዴዎችን በመጠቀም የተማሪዎችን የትምህርት ቅበላ በተከታታይ መመዘን፣

- ተማሪዎች በተከታታይ ምዘና ያገኟቸውን ውጤቶች በአግባቡ መዝግቦ መያዝ፣

- ውጤቶችን መሠረት በማድረግም የተሻለ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች ማበረታታት፣ ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ተማሪዎች መርዳት፣ በዓመቱ መጨረሻ ተማሪዎች በየትምህርት ዓይነቱ ያገኙትን ውጤት በሮስተር ላይ በሁለት ኮፒ ሞልቶ አንደኛውን ኮፒ ለጣቢያው በማስቀረት ሁለተኛውን ኮፒ ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት መላክ፣

- ሥርዓተ ትምህርቱንና የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ መሠረት ያደረገ ዓመታዊ፣ ወርሃዊ፣ ሣምንታዊና እለታዊ የትምህርት እቅድ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ፣

- ሕብረተሰቡ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት እንዲልክ በትምህርት ሥራ በንቃት እንዲሳተፍ ከጣቢያ አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር በጋራ መስራት፣

- የሴት ተማሪዎችን ተሣትፎ ለማሳደግ የተለያዩ ሥልቶችን ቀይሶ ተግባራዊ ማድረግ፣

- በአካባቢው የሚገኙ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ሕብረተሰቡን መቀስቀስ፣

- ለመማር ማስተማር ሥራ የሚጠቀምባቸውን ቁሳቁሶች በአግባቡ መያዝና በቁጠባ መጠቀም፣
- የአካባቢውን ሕብረተሰብ ባሕልና ወግ ማክበርና ለተማሪዎችም አርአያ ሆኖ መታየት፣

- የትምህርቱን ሥራ አፈፃፀም ወቅታዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለወረዳ ትም/ጽ/ቤት መላክ፡፡

- ወደ ክፍል ከመግባቱ (ቷ) በፊት በሚሰጠው ትምህርት ላይ በቂ ዝግጅት ማድረግና የተለያዩ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎችን መጠቀም፣





- በክልልና በወረዳ ደረጃ በሚዘጋጁ ልዩ ልዩ ሥልጠናዎችና የምክክር ስብሰባዎች ላይ ተገኝቶ ንቁ ተሣትፎ ማድረግና የቀሰሙትን አዲስ እውቀትና ተሞክሮ ተግባራዊ ማድረግ፣

## 8. የአመቻቾች ደመወዝና ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች

- የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አመቻቾች ሥራቸውን የሚያከናውኑት ከሕብረተሰቡ ጋር ከቦታ ቦታ በመንቀሳቀስ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት አመቻቾች በሥራቸው ላይ ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩና ውጤታማ እንዲሆኑ ፣ ፈታኝ የሆነውንና የሥራቸውን ሁኔታ ያገናዘበ እንዲሁም ሊያሰራ የሚችል (ከድካማቸው ጋር የሚመጣጠን) የወር ደመወዝና ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችን ማግኘት ይገባቸዋል፡፡

- የአመቻቾች ወርሃዊ ደመወዝ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ በምክር ቤት ወይም በት/ቢሮ በክልል ደረጃ ተወስኖ በወረዳ ትም/ጽ/ቤት በጀት ተይዞለት በወቅቱ የሚከፈል ይሆናል፡፡

- ከወርሃዊ ደመወዝ በተጨማሪ አመቻቾች እንደ ሥራ ትጋታቸው ልዩ ልዩ ማበረታቻዎች የሚያገኙበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ የሚሰጠው ማበረታቻም እንደአስፈላጊቱ በገንዘብ፣ በዓይነትና በአገልግሎት ወዘተ

ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንን የማበረታቻ አሰጣጥ የጣቢያ ትምህርት አመራር ኮሚቴው ያስተባብራል፡፡

- አመቻቾች የትምህርት ደረጃቸውን በየጊዜው የሚያሻሽሉበት ስልት በክልሉ ት/ቢሮ ተነድፎ ተግባራዊ ይደረጋል፤

## 9. የትምህርት ድጋፍና ክትትል

የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ጥራትና አቻነት ለመጠበቅ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃና አነስተኛ ሥልጠና ላላቸው አመቻቾች ተከታታይ የሆነ የቅርብ የሱፐርቪዥን ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ ማመቻቸት ለትምህርቱ ሥራ ቁልፍ ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በየደረጃው ያሉ የትምህርት አካላት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

### 9.1. በክልል ትምህርት ቢሮ ደረጃ

- የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ውጤታማ እንዲሆን በትምህርት ፕሮግራሞችና ሱፐርቪዥን መምሪያ ወይም አግባብ ባለው የሥራ ሂደት ሥር የተጠናከረ የሱፐርቪዥን የክትትልና ግምገማ ሥርዓት ይዘረጋሉ፡፡ ለዚህም በቂ ባለሙያዎችና በጀት ይመድባሉ፡፡ ባለሙያዎቹም በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም አተገባበር፣ የሱፐርቪዥን ክትትልና ግምገማ ላይ ብቁ ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋሉ፡፡ በተመሳሳይም በወረዳ ደረጃ ላሉ ባለሙያዎች ተመሳሳይ ሥልጠና በመስጠት አቅማቸው እንዲገነባ ያደርጋሉ፡፡ ፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴርም ከዚህ አኳያ አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ያደርጋል፡፡





- ተንቀሳቃሽ ትምህርት አዲስ በመሆኑና በባሕሪው ውስብስብና ለአመራርም አስቸጋሪ በመሆኑ ፕሮግራሙ በቀላሉ እንዳይከሽፍ (እንዳይወድቅ) የክልል ትም/ቢሮዎች የቅርብ ክትትልና የተለየ የማቴሪያልና የሙያ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡
- መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅቶች የሚያካሄዱትን ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ጥራት፣ ተገቢነትና ደረጃውን ጠብቆ በክልል በተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት መካሄዱን በየጊዜው ይቆጣጠራሉ፣ ሙያዊ እገዛም ይሰጣሉ፡፡

- በክትትልና ግምገማ ያገ˜ቸውን ግብረ መልሶች በግብዓትነት በመጠቀም ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የሚሻሻልበትና የሚጠናከርበትን ስልቶች እያጠኑ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡

- ከወረዳዎች ጋር በመመካከር ሞዴል ተንቀሳቃሽ አማራጭ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ይመርጣሉ፣ ያጠናክራሉ የልምድ ልውውጥ ያካሂዳሉ፣ መልካም ተሞክሮዎችንም በመቀመር ለሌሎች ያስተላልፋሉ።

### 9.2 በወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ደረጃ

የወረዳ ትም/ጽ/ቤቶች ከመደበኛውና ከቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራሞች እኩል ትኩረት የሚሰጥ የሱፐርቪዥን መርሃ ግብር አዘጋጅተው በሁሉም ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ት/ቤቶች ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ በዚህም መሠረት፣-

◊ የወረዳ ሱፐርቫይዘሮች ቢቻል በወር አንድ ጊዜ ካልሆነ ግን በየሁለት ወር በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች በአካል በመገኘት ለአመቻቾች ተገቢውን ሙያዊ ድጋፍ (በትምህርት እቅድ ዝግጅት፣ በትምህርት አቀራረብ፣ በተማሪ ሪከርድ አያያዝ ወዘተ) ያደርጋሉ፡፡ የጣቢያ ትምህርት አመራር ኮሚቴውን በማነጋገርና በችግሮች ላይ በመወያየት የጋራ መፍትሄ ይሻሉ፡፡ በቦታው ሊፈቱ ያልቻሉ ችግሮችን ወደ ወረዳ ትምህርት ጽ/ ቤት በማቅረብ መፍትሄ ያፈላልጋሉ።

◊ የትምህርት ጽ/ቤቶች የሱፐርቪዥን አገልግሎትን ተግባራዊ ለማድረግ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ እያንዳንዱ ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያ በምን ወቅት የት እንደሚገኝ ትክክለኛ መረጃ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ለዚህም በየአካባቢው ያሉ ባሕላዊ የመረጃ ልውውጥ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል።

◊ የሱፐርቪዥን አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የትራንስፖርትና ሌሎች ፋሲሊቲዎችን መሟላት አለባቸው፡፡

◊ ከክልል ትም/ቢሮ ጋር በመመካከር ሞዴል ተንቀሳቃሽ ትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ይመርጣሉ፣ ያጠናክራሉ፣ የልምድ ልውውጥ ያካሄዳሉ፡፡ መልካም ተሞክሮዎችንም በመቀመር ለሌሎች ያስፋፋሉ፡፡





◊ በወረዳው ውስጥ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያካሄዱትን ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ጥራትና ተገቢነት ደረጃውን ጠብቆ በክልል በተዘጋጀው ሥርዓተ ትምህርት መሠረት መካሄዱን በየጊዜው ይቆጣጠራሉ፣ ሙያዊ እገዛም ይሰጣሉ፡፡

◊

◊ ተጠቃሚውን ማህበረሰብ፣ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በማሳተፍ በየሩብ ዓመቱ የወረዳውን የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት እንቅስቃሴ ይገመግማሉ፣ ችግሮችን አንጥሮ በማውጣት የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣሉ፡፡

◊

◊ አንድ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መስጫ ጣቢያ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ በአቅራቢያው መደበኛ ትምህርት ባለበት አካባቢ ቆይታ የሚያደርግ ከሆነ መደበኛው ት/ቤት የሱፐርቪዥን፣ የሙያዊ እገዛና የመማሪያ ማስተማሪያ መርጃ መሣሪዎች ዝግጅት እገዛ ያደርግለታል፡፡ ይህንንም የወረዳው ትምህርት ፅሕፈት ቤት ያስተባብራል፡፡

◊ የአርብቶ አደሩ ሕብረተሰብ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ከመደበኛ መኖሪያ ወረዳው አልፎ ወደ ሌላ ሩቅ ወረዳ የሚያመራ ከሆነ የትምህርት ክትትልና ድጋፍ ሥራ ሕብረተሰቡ አዲስ በሰፈረበት ወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት አማካኝነት ይሰጣል፡፡

## 10. የባለድርሻዎች ትስስርና አጋርነት

የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የትምህርት ተሳትፎ አሁን ካለበት ዝቅተኛ ደረጃ የማሳደግና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን በ2008 ዓ.ም ለሁሉም ሕፃናት የማዳረሱ ግዙፍ ሥራ ለመንግሥት ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉንም ባለድርሻዎች ማለትም የአርብቶ አደር ማህበረሰቦችን፣በአርብቶ አደሩ ትምህርት ድርሻ ያላቸውን መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን የተቀናጀ ጥረትና መረባረብ የሚጠይቅ ነው።

ስለሆነም እንደሌሎቹ የአርብቶ አደር ትምህርት ኘሮግራሞች ሁሉ ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ፡-

- ዓለም አቀፍና ሀገር በቀል መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች
    - ◊ የኘሮግራሙን ተደራሽነት፣ ጥራትና ተገቢነት ከማረጋገጥ፣ እንዲሁም የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ከማሳደግ አኳያ የፋይናንስ የቁሳቁስና የቴክኒክ ድጋፍ በማድረግ፣
    - ◊ በመማሪያ-ማስተማሪያና በአመቻቾች ሥልጠና ሞጁሎች ዝግጅት በንቃት በመሳተፍና አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት
    - ◊ በክልል፣ በወረዳና በነጥብ ጣቢያ ደረጃ የአስፈፃሚ አካላትን አቅም በመገንባት





- ◊ በዕቅድ ዝግጅት ሂደት በንቃት በመሳተፍ፣ የእቅድ ድርሻን ወስዶ ተግባራዊ በማድረግና በዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በመካፈል፣
- ◊ ኘሮግራሙ አፈፃፀም ላይ በሚታዩ ችግሮች ላይ የጥናትና ምርምር ሥራዎችን በማካሄድና ተጨባጭ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማቅረብ፣
- ◊ በኘሮግራሙ ዙሪያ መረጃዎችንና ተሞክሮዎችን በመለዋወጥ ወዘተ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይጠበቅባቸዋል፤

- በየደረጃው የሚገኙ ትምህርት መዋቅሮች ማለት የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር፣ የክልል ትምህርት ቢሮዎችና የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤቶች የተለያዩ ባለድርሻዎች ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን አስተዋጽኦዎች ያበረክቱ ዘንድ ምቹ ሁኔታዎችን የመፍጠር፣ የማስተባበርና አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው።

## 11. የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አመራር፣ አደረጃጀትና የሕብረተሰብ ተሣትፎ፤

### 11.1 በየደረጃው ያሉ የትምህርት መዋቅር አካላት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት በአርብቶ አደር አካባቢዎች በመካሄድ ላይ ያሉ የትምህርት ኘሮግራሞች አካል ነው። ስለሆነም ኘሮግራሙ በ1994 ዓ.ም በት/ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ ክልሎች ከተጨባጭ ሁኔታዎቸው ጋር አገናዝበው እየሰሩበት ባለው የትምህርት አመራርና አደረጃጀት መመሪያ መሠረት የሚካሄድ እንጂ የራሱ የተለየ መዋቅርና አደረጃጀት የሚያስፈልገው አይደለም። ስለሆነም ኘሮግራሙን በተመለከተ በየደረጃው ያሉ የትምህርት መዋቅር አካላት የሥራ ድርሻና ኃላፊነት ከዚህ እንደሚከተለው ቀርቧል።

#### 11.1.1. የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

- የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም የጥራት ደረጃውን በጠበቀና ወጥነት ባለው መንገድ እንዲካሄድ የአተገባበር መመሪያ ያወጣል፤ መመሪያው ከአርብቶ አደር አካባቢዎች ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፤ በአፈፃፀሙ ሂደት አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል።

- ለኘሮግራሙ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማሟላት በክልል ደረጃ የሚደረጉ ጥረቶችን ከማገዝ አኳያ ሀብት የማፈላለግ ሥራዎችን ያከናውናል፤





- በመማሪያ-ማስተማሪያና በስልጠና ሞጁሎች ዝግጅት፣ በአመቻቾች ሥልጠና፣ በኘሮግራሙ አተገባበር ወዘተ ላይ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የክልል ሀላፊዎችና ባለሙያዎች የተለያዩ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

- በኘሮግራሙ አፈፃፀም ላይ እስከወረዳና ነጥብ ጣቢያ ድረስ የሚዘልቅ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፣

- የኘሮግራሙን አፈፃፀም ከክልል ባለድርሻዎች ጋር በየጊዜው ይገመግማል፤ ኘሮግራሙን የሚጠናከሩ ስልቶችን በጋራ ይነድፋል፤ ለተግባራዊነታቸውም አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፤

- ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክልሎች መካከል የልምድ ልውውጥ መድረኮችን ያዘጋጃል፤ አርአያነት ያላቸውን ተሞክሮዎች ይቀምራል፣ ያሰራጫል

#### 11.1.2 የክልል ትምህርት ቢሮ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

- በክልሉ የሚካሄደውን ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም በበላይነት ይመራል፣ ያስተባበራል፣ ይፈጽማል፡፡

- በማዕከል የተዘጋጀውን ይህን የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት አተገባበር መመሪያ ከክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማጣጣም ተግባራዊ ይደረጋል።

- ለአርብቶ አደሩ የተዘጋጀውን የቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መርሃ ትምህርት መነሻ በማድረግና የሚመለከታቸውን ባለድርሻዎች በማሳተፍ በየትምህርት ዓይነቱ የመማሪያ ማስተማሪያ ሞጁሎችን ያዘጋጃል፡፡ ሞጁሎቹ የአርብቶ አደሩን ተጨባጭ የኑሮ ሁኔታ የሚያንፀባርቁ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

- ከወረዳዎች ጋር በመነጋገር በተመረጠ የመም/ትም/ኮሌጅ ውስጥ ተገቢው አደረጃጀት እንዲፈጠር በማድረግ የአመቻቾች የቅድመ-ሥራና የሥራ ላይ ሥልጠና እንዲሁም የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ሥልጠና እንዲሰጥ ያደርጋል፤ ሥልጠናዎቹን ያስተባብራል አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርትን ለሚያስፈጽሙ የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን ይሰጣል፤

- አግባብ ያላቸውን ባለድርሻዎች በማሳተፍ የትምህርት ኘሮግራሙንና የመማር ማስተማሩን ሂደት በጋራ ይገመግማል። በአፈፃፀም ላይ ያጋጠሙ ችግሮች የሚቃለሉበትን ስልት እየነደፈና ሥራ ላይ እንዲውል እያደረገ ኘሮግራሙን ያጠናክራል።

- በክልሉ ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም ለጀመሩና መጀመር ለሚፈልጉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተገቢውን መረጃና





ድጋፍ ይሰጣል፤ ኘሮግራሙ መመሪያን ጠብቆ በቅንጅት መካሄዱን ያረጋግጣል፤

- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራምን ያጠናቀቁ ተማሪዎች በመደበኛው ትምህርት 5ኛ ክፍል ገብተው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ስልት ነድፎ ለተግባራዊነቱ ይንቀሳቀሳል፡፡

### 11.1.3 የዞን ትምህርት መምሪያ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት

- በዞኑ የሚካሄደውን ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ኘሮግራም ያስተባብራል፤ ሙያዊና ቴክኒካዊ ድጋፍም ይሰጣል፤

- የመማሪያ - ማስተማሪያ መፃሕፍት፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችንና ቁሳቁሶችን ስርጭት ያስተባብራል።

- የክልሉ ትምህርት ቢሮ በሚሰጠው ኃላፊነት መሠረት በወረዳዎች ሊፈፀሙ የማይችሉ ተግባራትን ያከናውናል።

### 11.1. 4 የወረዳ ትም/ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

- በወረዳው ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ፣ እንዲስፋፉ ያደርጋል፡፡

- በጣቢያዎቹ የሚሰጠው ትምህርት የአካባቢውን ህብረተሰብ ባህልና አኗኗር መሠረት ያደረገ እና ከአርብቶ አደሩ ህይወት ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡

- በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎቹ ለማስተማር የሚመረጡት አመቻቾች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተጠቀሱት መመዘኛዎች መሠረት መመረጣቸውን ያረጋግጣል።
- ከት/ቢሮ ጋር በመነጋገር ለአመቻቾች ተከታታይ የሥራ ላይ ሥልጠናዎች እንዲሰጡ ያደርጋል።
- አመቻቾች ማግኘት የሚገባቸውን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በወቅቱ እንዲያኙ ያደርጋል፡፡
- የመማር ማስተማሩ ሂደት ውጤታማ እንዲሆን ስልት በመንደፍ ለተግባራዊነቱ ክትትል ያደርጋል፡፡
- ለተንቀሳቃሽ ጣቢያዎች የሚያገለግሉ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ከአካባቢው ከሚገኙ ማቴሪያሎች እንዲዘጋጁ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል።
- በወረዳው ያሉ ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያዎች የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት መድረክ ያዘጋጃል።
- በወረዳው በተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ሥራ ላይ





የተሰማሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ማህበራት በቅንጅት የሚሰሩበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

- መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማስተባበር የመማር ማስተማሩ ተግባር እንዲጠናከር ያደርጋል፡፡
- በመማር ላይ የሚገኙ ተማሪዎች ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ ልዩ ልዩ ዘዴዎችን ይቀይሳል፤ ባለድርሻ አካላትን በማስተባበርም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ፕሮግራምን የሚመለከቱ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን፣ የተማሪዎች ሮስተሮችን የአመቻቾች የግል ፋይሎችን ወዘተ በአግባቡ አደራጅቶ ይይዛል። የፕሮግራሙን አፈፃፀም የሚመለከቱ ወቅታዊ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለክልል ትምህርት ቢሮ ይልካል፤

### 11.1.5 የጣቢያ ትምህርትና ሥልጠና አመራር ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

- የትምህርት መስጫ ጣቢያው ንብረት ከቦታ ቦታ ሲንቀሳቀስ እንዳይበላሽ፣ በአንክብካቤ በአካባቢው እንዲያዝና ለትምህርት ሥራ እንዲውል በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡
- ተንቀሳቃሽ ጣቢያዎች እንዲቋቋሙ ከወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት፣ ከቀበሌና ከጎሳ መሪዎች ጋር በመሆን ይሰራል፡፡
- ለተንቀሳቃሽ ህብረተሰብ የሚስማማ የትምህርት መስጫ ጊዜ እና ቦታ

ከአመቻቾችና ከተጠቃሚው ህብረተሰብ ጋር በመሆን ይመርጣል፡፡

- የሚሰጠው ትምህርት ከህብረተሰቡ ባህልና አኗኗር ጋር የተጣጣመ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡
- የሚመረጡት አመቻቾች ከህብረተሰቡ ውጪ የተገኙ ከሆነ የህብረተሰቡን ባህል፣ ወግና አኗኗር ጠንቅቀው የሚያውቁ መሆናቸውን በማረጋገጥ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን ይመለምላል፡፡
- አመቻቾች በሥራ ላይ እንዲቆዩ የተለያዩ የማበረታቻ ስልቶችን ነድፎ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
- ቀላልና ከቦታ ቦታ መንቀሳቀስ የሚችሉ የመማሪያ ክፍሎች ከአካባቢ ከሚገኙ ማቴሪያሎች እንዲሰሩ ያስተባብራል፡፡
- ሴት ተማሪዎች እንዲማሩ የተለየ ትኩረትና እገዛ ያደረጋል፡፡
- አመቻቾች የመማር ማስተማሩን ሂደት በአግባቡ መምራታቸውን ይከታተላል፡፡
- ኃላፊነቱን (ቷን)በማይወጣ/በማትወጣ አመቻች ላይ እንደጥፋቱ ደረጃ ውሳኔ ይሰጣል፤
- ድርቅና ርሃብን በዘላቂነት ለመቋቋም ተማሪዎች ከወዲሁ የሥራ ፍቅር ኖሯቸው እንዲያድጉ ምሳሌ ይሆናል።





- ኮሚቴው ቢያንስ በየ15 ቀኑ እየተሰበሰበ በትምህርት ሥራ ላይ ውይይት ያደርጋል፡፡
- የተንቀሳቃሽ ትምህርት ቤት (ነጥብ ጣቢያ) ትምህርትና ሥልጠና አመራር ኮሚቴ አካላት፡-
    - በማህበረሰቡ የሚመረጥ .............. ሰብሳቢ
    - የሃይማኖት መሪ 2 ወይም 3 ...... አባላት
    - አመቻች ...................................... አባል
    - ሁለት የወላጅ ተወካዮች (አንድ ሴትና አንድ ወንድ).... አባሎች

### 11.2 የሕብረተሰብ ተሳትፎ

አገራችን ከምትከተለው ያልተማከለ የትምህርት አደረጃጀትና አመራር አኳያ ሕብረተሰቡ በትምህርት ሥራ እንዲጫወት የሚጠበቅበት ሚና ከፍተኛ ነው። በተለይም በት/ቤት (በትምህርት መስጫ ጣቢያ) ደረጃ ህብረተሰቡ የት/ቤቶችን (ጣቢያዎችን) ግንባታ በጉልበቱ፣ በገንዘቡ፣ በቁሳቁስና በእውቀት ከማገዝ አንስቶ የትምህርቱን የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት እስከ መምራትና መቆጣጠር የሚደርስ ሰፊ ተሳትፎ ሊኖረው እንደሚገባ ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የዋለው "የትምህርት አመራር፣ አደረጃጀት፣ የህብረተሰብ ተሳትፎና የፋይናንስ መመሪያ" ያመለክታል።

የህብረተሰብ ተሳትፎ ጥያቄ በአርብቶ አደር አካባቢዎች ከሚካሄደው ተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም አኳያ ሲታይ የፕሮግራሙን ህልውና

የሚወስን መሠረታዊ ጥያቄ ሆኖ እናገኘዋለን። ለዚህም ዋናው ምክንያት ከፕሮግራሙ ተንቀሳቃሽ ባህሪይ የሚመነጩ ተግባራትና ኃላፊነቶች የተጠቃሚውን ማህበረሰብ ሁለገብ ተሳትፎ የግድ አስፈላጊ ስለሚያደርጉት ነው። ስለሆነም ማህበረሰቡ ይህን እውነታ በሚገባ ተገንዝቦ ከፕሮግራሙ ቅድመ ዝግጅት እስከ ትግበራ ባለው ሂደት ውስጥ፡-

- ኃላፊነታቸውን በብቃት ሲወጡ የሚችሉ የጣቢያ ትምህርት አመራር ኮሚቴ አባላትን በመምረጥና ለኮሚቴው ሥራ መቃናት አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት፣
- በአመቻቾች ምልመላ በንቃት በመሳተፍ፣
- በቀላሉ ከቦታ ቦታ ሊጓጓዙ ከሚችሉ የአካባቢ ቁሳቁሶች የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን በመስራት (በድንኳን መጠቀም ካልተቻለ)፣
- የትምህርት መስጫ ጣቢያዎችን ለትምህርት ምቹ በማድረግ፣
- የትምህርት መስጫ ቦታና ጊዜን በመወሰን፣
- ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሰ ወንድና ሴት ልጆችን ወደ ትምህርት መስጫ ጣቢያ በመላክና ትምህርታቸውን እንዳያቋርጡ በማድረግ፣





- የትምህርት መስጫ ጣቢያን፣ የትምህርት ቁሳቁሶችን፣ አመቻቾችንና የግል ቁሳቁሳቸውን ከቦታ ቦታ ማጓጓዣ እንስሳትን በማቅረብ እንዲሁም የትምህርት መስጫ ጣቢያን በመድረሻ ቦታ ላይ በማቋቋምና በማደራጀት፣
- የትምህርት መስጫ ጣቢያው የሚገኝበትን ቦታና የቆይታ ጊዜ የሚመለከቱ መረጃዎችን በየወቅቱ ለወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት በመስጠት፣
- በጣቢያው የትምህርት ዕቅድ እና የዕቅድ አፈፃፀም ግምገማ በንቃት በመሳተፍ፣
- ለአመቻቾች መጠለያ በማዘጋጀት፣ ደህንነታቸውን በመጠበቅና አስፈላጊውን ድጋፍ በመስጠት /ምሳሌ፣አመቻቾች የራሳቸው የእርባታ እንስሳት ካላቸው እንስሳቱን በመጠበቅ/፣
- የሥራ ኃላፊነታቸውን በሚገባ ለሚወጡ አመቻቾች ማበረታቻ በመስጠት፣
- በጣቢያው የሚሰጠውን ትምህርት ጥራት ለመጠበቅና ለማጠናከር አቅም የሚፈቅደውን ድጋፍ በገንዘብ ወይም በዓይነት በመስጠት የበኩሉን አስተዋጽኦ በሙሉ ፈቃደኝነት

ማበርከት ይጠበቅበታል፡፡ ለዚህም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት /የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት፣ የወረዳ ምክር ቤት፣ ወዘተ/ ተከታታይ ያላቸዉ የቅስቀሳና የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን የማከናወን ኃላፊነት አለባቸው፡፡




# ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም !!!